# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በግብርና ሚኒስቴር

## ከግብርና ኤክስቴንሽን በተለይ የሰብል ኤክስቴንሽን አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት



*ሚያዝያ 2007 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*

# ማውጫ

**ክፍል አንድ** ........ **1**

**መግቢያ** ........ **1**

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ........ 2

ራዕይ ........ 2

ተልዕኮ ........ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ........ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........ 4

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 4

የሰው ኃይል ........ 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........ 5

የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 6

**ክፍል ሁለት** ........ **8**

**የኦዲት ግኝቶች** ........ **8**

2.1. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ፣ የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህልና የዕውቀት ደረጃ መሰረት በማድረግ በስልጠና የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 8

በተለያየ ስነ ምህዳር የኤክስቴንሽን አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤ ........ 8

ለኢንዱስትሪ የሚሆን ምርት እንዲመረትና የኢንዱስትሪ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፤ ........ 9

የአርሶ አደሩን ዘመናዊ አሰራሮችንና የግብርና ምርቶች ተጠቅሞ የማምረት ፍላጎት ግንዛቤ ለማሳደግ ዕቅድ ታቅዶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 11

የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ያሉ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎችን በተመለከተ፤ ........ 13

የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከል እንዲደራጅ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 14

በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ለአርሶ አደሩ በብቃት አህድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እና ለልማት ሰራተኞች የብቃት ማረጋገጫ መሰጠቱን በተመለከተ፤ ........ 16

2.2 ለአርሶ አደሩ የተሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶለት ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 19

የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 19

አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በማደራጀት አተገባበሩን በማየት ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 20
በተሰበሰቡና በተቀመሩ ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት ስለመስጠቱ፤ ........ 22
የሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ላይ የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤ ........ 25
ደረጃዎችን በማውጣት በደረጃው መሰረት የአርሶ አደር ማሰልጠኛዎቹ እንዲሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 26
አርሶ አደሩ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 27
2.3 የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት በድህረ ገፅና መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ........ 31
ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን አቅርቦት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 31
የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው መመስረታቸውንና በቅንጅት መስራታቸውን በተመለከተ፤ ........ 32
አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት እንዲሁም በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ ያለውን ድጋፍ በተመለከተ፤ ........ 34
በኤክስቴንሽን አፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት አውደ ጥናት መካሄዱን ግብረ መልስ መሰብሰቡንና ጥናት መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 36
**ክፍል ሶስት ........ 39**
**መደምደሚያ ........ 39**
**ክፍል አራት ........ 43**
**የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 43**
አባሪ 1 ........ I
የግብርና ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር ........ I
አባሪ 2 ........ II
የኦዲትመመዘኛመስፈርቶች (EVALUATIVE CRITERIA) ........ II
አባሪ 3 ........ V
በናሙና የታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ዝርዝር ........ V

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

1. ኢትዮጵያ በዋናነት ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ ከመሰረቱ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ እድሜው ለስራ ከደረሰው ህዝብ 80 እስከ 85 በመቶ የሚሆነው የተሰማራው በግብርና ላይ ነው፡፡ እንዲሁም 47 በመቶ የሚሆነው የሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (GDP) እና ከ80 ከመቶ በላይ የሚሆነው የውጭ ምንዛሬ የሚገኘው ከዚህ ዘርፍ ነው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አገራችን በምግብ ሰብል ለሌሎች መካከለኛና ምስራቅ አፍሪካ አገሮችን ለመመገብ የሚያስችል ዕምቅ ሀብት አላት፡፡ ግብርናን በሚመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት የእርሻ የመስሪያ ቤት ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በ1900 ዓ.ም የተቋቋመ የመንግስት ተቋም ነበር፡፡ በመቀጠልም በተለያዩ መጠሪያዎች አደረጃጀቶችና ስሞች ሲጠራ ቆይቶ አሁን የያዘውን መጠሪያ በ2003 ዓ.ም አግኝቷል፡፡
2. በተለያየ የሀገሪቱ ክፍለ ግዛቶች የግብርና ምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በስፋት ለማዳረስ ሲባል ከውጭ ሀገር በተገኘ እርዳታ እ.አ.አ. በ1960ዎቹ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ተቀረጹ፡፡ እነዚህም በ1963 የመጀመሪያው መለስተኛ የእርሻ ልማት ፕሮጀክት በመቀጠል ደግሞ በ1972 ሁለተኛው የእርሻ ልማት ፕሮጀክት የተቋቋመ ሲሆን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በውስን መልኩም ቢሆን ለማሳደግ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የፕሮጀክቶቹ ጊዜ ሲያበቃ ይህንን ሊያስቀጥል የሚችል በጀትና ድጋፍ ከመንግስት ባለመኖሩ ቀጣይነት ሊኖረው አልቻለም፡፡ በኋላም በ1980 ዓ.ም አካባቢ በአንዳንድ ጉዳዩ ባሳሰባቸው የግብርና ባለሙያዎችና ባለስልጣናት አነሳሽነት የምርምር ኤክስቴንሽን አገናኝ ኮሚቴ በአገር አቀፍና በዞን ደረጃ እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ ነገር ግን አገናኝ ኮሚቴው ገና ስራውን ሲጀምር ከፍተኛ መነሳሳትን የፈጠረ ቢሆንም በወቅቱ በተደረገው የመንግስት መ/ቤቶች ለውጥና በባለሙያዎች ሽግሽግ የተነሳ የታሰበውን ፋይዳ ሳይሰጥ ለተወሰኑ አመታት ተቋርጦ ቆይቷል፡፡
3. የግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት አሠጣጥ አስተዳደርን በተመለከተ በየጊዜው በተለያዩ ተቋማት በግብርና ኮሌጅ፤ በግብርና ሚኒስቴር በሌላ ጊዜ ደግሞ በግብርና ምርምር ተቋማት ስር እንዲዋቀር እና በፕሮጀክቶች እንዲደገፍ በመደረጉና ወጥ የሆነ አወቃቀርና አደረጃጀት ሥርዓት እንዲሁም በባለቤትነት የሚያንቀሳቅስ አካል ባለመኖሩ

የኤክስቴንሽን አገልግሎቱና የልማት አካላት ግንኙነት የተዳከመ ሆኖ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት በግብርና ሚኒስቴር ስር ራሱን ችሎ በዳይሬክቶሬት ደረጃ እንዲቋቋምና የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ተደርጓል።

4. ግብርና ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የተቋቋመ ሲሆን፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ለግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ተጠሪ ከሆኑ አራት ሚኒስቴር ዴኤታዎች አንዱ በሆነው በግብርና ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ስር የሚገኝ ዳይሬክቶሬት ነው።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

5. "በገበያ የሚመራ ዘመናዊ ግብርናና ከድህነት የተላቀቀ ህብረተሰብ መፍጠር"

### ተልዕኮ

6. 'ህብረተሰቡን ከድህነት ለማላቀቅ የሚያስችል የላቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀምና ከፍተኛ ምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ የግብርና ስርዓት መፈጠር' የሚል ተልዕኮ አለው። ይህንን ተልዕኮ ለማስፈጸም እንዲረዳው፡-

- ✓ በገበያ የሚመራ ዘመናዊ የግብርና ዘዴ ማስፋት፣
- ✓ የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ፣ ማልማትና በዘላቂነት ጥቅም ላይ ማዋል፣
- ✓ ዘመናዊ የግብርና ግብይት ሥርዓትን መዘርጋት፣
- ✓ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅምን ማጎልበት እና
- ✓ ሴቶችንና ወጣቶችን ለልማት ማብቃትና ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

7. የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል።

- ✓ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ እና ለግል ባለሀብቱ የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የስልጠና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- ✓ ለገበያ የሚቀርብ የግብርና ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

- ✓ ወደ ሀገር በሚገቡም ሆነ ከሀገር በሚወጡ ዕፅዋት፣ አዝርዕት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ላይ የኳረንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤
- ✓ የእንስሳትና የዕፅዋት በሽታዎች ወረርሽኝንና ተዛማች ተባዮች ይከላከላል፤
- ✓ የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂ የግብርና ልማት የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ✓ የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን ይገነባል፣ አቅርቦቱን ያረጋግጣል፤
- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካሎችና የእንስሳት መድሀኒቶች አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤
- ✓ የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤
- ✓ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ሥራዎችን ያከናውናል፤ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም መተግበሩን ያረጋግጣል፤
- ✓ የብድር አገልግሎቶች ለአርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች የሚቀርቡበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል፤
- ✓ በግብርና ምርት ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይከታተላል፤ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ የግብርና ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ ለግብርና ልማት አጋዥ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- ✓ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደረጃል፤
- ✓ የግብርና ምርምርን፣ የብዝሀ ህይወት ጥበቃን እና ከክልሎች በተገኘ ውክልና መሰረት በፌደራል መንግስት ሥር እንዲሆኑ የተደረጉ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬቶችን አስተዳደር የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሚኒስትርና በአራት ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን፣ በሚኒስትሩ ስር አራት ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ ለሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ ስምንት ዳይሬክትሬቶች፣ አንድ ማዕከልና አንድ ጽ/ቤት ሲኖሩ በግብርና ልማት ዘርፍ ስር 11፣ በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ሥር 3፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ሥር 3 እና በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ሥር 2 ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በነሐሴ ወር 2006 ዓ.ም 410 (34%) ሴት ሰራተኞች 787 (66%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 1197 የቋሚ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን፣ በተጨማሪም 261 ኮንትራት ሰራተኞች ነበሩት፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የቋሚ ሰራተኞች የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ፒኤችዲ 4 (0.003%)፣ ሁለተኛ ዲግሪ 73 (6%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 306 (26%)፣ ዲፕሎማ 216 (18%) እና ከዛ በታች ያሉ 598 (50%) ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

10. ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት በሚመደብለት ሲሆን ከ2004-2006 ድረስ የተመደበለት በጀትና ስራ ላይ የዋለው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2004 | መደበኛ | 201,184,112.33 | 887,695,005.72 | 441% |
| | ካፒታል | 2,396,392,600.00 | 2,348,907,174.74 | 98% |
| 2005 | መደበኛ | 1,009,418,181.98 | 973,985,445.34 | 96.49% |
| | ካፒታል | 586,329,606.19 | 561,926,632.72 | 95.84% |
| 2006 | መደበኛ | 704,499,020.20 | 660,002,442.36 | 93.68% |
| | ካፒታል | 579,864,635.85 | 572,499,676.69 | 98.73% |

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም ሀገሪቱ ካላት የግብርናን ፈጣን ዕድገት በዘላቂነት የማረጋገጥ እና የግብርናን ምርትና ምርትማነት የማሳደግ ራዕይ አንፃር ግብርና ኤክስቴንሽኑ ለአርሶ አደሩ ዘመናዊና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋት ለመጠቀም የሚያስችል የክህሎት ስልጠና፣ የምክር አገልግሎት የገበያና ሌሎች መረጃዎችን መስጠቱንና ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን እንዲሁም በልማት አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር መደረጉን በመገምገም የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ **በግብርና ኤክስቴንሽን በተለይ ሰብል ኤክስቴንሽን** አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

13. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፥
    1. የሰብል ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ወጥ ተከታታይነት ያለው መሆኑን፣ እንዲሁም የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤና ባህል እንዲሁም የዕውቀት ደረጃ መሰረት ያደረገና በስልጠና የተደገፈ መሆኑን መገምገም፤
    2. ለአርሶ አደሩ የተሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶለት ወጥና በሪፖርት የተደገፈ እንዲሁም ግብረ መልስ የሚሰጥበት መሆኑን ማረጋገጥ፤
    3. የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ የመረጃ አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በድህረ ገፅና መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ማሰራጨቱን፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ያሉ የስራ ክፍሎች በመረጃ

ተናበው መስራታቸውን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው።

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

14. ከላይ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 25 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተው ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል። የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊነት፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና አመታዊ ዕቅድ፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ሥርዓቶች፣ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው። የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል።

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2004-2007 ሩብ በጀት አመት ያሉትን የሥራ ክንውኖች ነው፡፡

16. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፣ በናሙና በተመረጡ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልሎች በሚገኙ፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት በመገኘት ለሚመለከታቸው ሰራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ ከግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ በማየት ነው። በናሙና ተመርጠው የታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል።

## የግብርና ኤክስቴንሽን ወሳኝ የሥራ ሂደት የሥራ ፍሰት መግለጫ

## (System Description)

17. የግብርና ኤክስቴንሽን ወሳኝ የሥራ ሂደት መነሻው የህብረተሰብ የግብርና ቴክኖሎጂ ፍላጎትና ችግር፣ ስትራቴጂክ ዕቅድና የልማት ትብብር ጥያቄ ሲሆን፣ በህብረተሰቡ ችግርና ፍላጎት ላይ የዳሰሳ ጥናት ይከናወናል፤ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስትራቴጂው እንዲተገበር የመምራትና የመደገፍ ሥራ ይሰራል፤ የልማት ትብብር ጥያቄ የመቀበልና ምክር የመስጠት እንዲሁም ፕሮግራም/ፕሮጀክት የመቅረፅ ስራ ይከናወናል፡፡
18. የልማት ትብብር ጥያቄ መቀበል ምክር መስጠት እንዲሁም ፕሮግራም/ፕሮጀክት መቅረፅ በሚለው ሥራ ላይ የተቀረፁት ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ መከታተል እንዲሁም ስልጠናና ድጋፍ መስጠት ከዚያም አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን መከታተልና በመረጃ ስርዓቱ መሰረት ለሚመለከተው የማሳወቅ ሥራ ይሰራል፡፡ በመጨረሻ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ግምገማ ይደረጋል፡፡
19. የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስትራቴጂ እንዲተገበር በመምራትና በመደገፍ የሥራ ሂደት ላይ ውጤታማ እንዲሆን አፈፃፀሙን መከታተልና መተግበር በመጨረሻም ብቁ የልማት ባለሙያ ማፍራት ነው፡፡
20. በህብረተሰቡ ችግርና ፍላጎት ላይ የደሰሳ ጥናት ከተሰራ በኋላ የግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኤክስቴንሽን ስርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር እንዲሁም ህብረተሰቡ ለልማት እንዲነሳሳና በኤክስቴንሽን ቡድን እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ የተለያዩ ለግብርናው አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በማካተት የግብርና ፓኬጅ ዝግጅትና ትግበራ ይከናወናል፡፡ ከዚህም በመቀጠል የልማት ክትትል ከቅድመና ከድህረ ምርት መረጃ በመነሳት ይከናወናል፡፡ በመረጃ ስርዓቱ መሰረትም ለሚመለከተው የማሳወቅ ሥራ ይኖራል፡፡ በመጨረሻ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ግምገማ በስራ ሂደቱ ፍሰት ላይ መነሻ ከተደረጉ ነጥቦቹ ጋር በማመሳከር አፈፃፀሙ ይታያል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ፣ የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህልና የዕውቀት ደረጃ መሰረት በማድረግ በስልጠና የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፣

### በተለያየ ስነ ምህዳር የኤክስቴንሽን አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤

21. በተለያየ ስነ ምህዳር ውስጥ ለሚገኙ አርሶ አደሮች የአካበቢውን ስነ ምህዳር መሰረት ያደረገ የግብርና አመራረት ዘይቤንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አካባቢ ተኮር የኤክስቴንሽን ስልት ተቀይሶ ሊተገበር ይገባል፡፡
22. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-
    - ✓ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በግራር ጃርሶ ወረዳ ኮትቾ ሶፋኒ ቀበሌ አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል አካባቢው ከባህር በላይ ከፍታ 2,700 ሜትር በመሆኑ የተካሄደው የጤፍ መዝራት ሙከራ መዘራት ባለበት የመስመር ርቀት መጠን አለመሆኑ እንዲሁም የተዘራው ዘር ከአካባቢው ዝርያ የማይሻልና ለአግሮ ኢኮሎጂው ተስማሚ አለመሆኑን፣
    - ✓ በምሥራቅ ኦሮሚያ ምዕራብ ሐረርጌ ዞን የአርሶ አደሮች እና የባለሙያዎች ስልጠና የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ አዘገጃጀት የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር ተከትሎ የበልግ እና የመኸር እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ወቅትን ያገናዘበ አለመሆኑን በመግለጽ ዞኑ በተደጋጋሚ ለክልሉ ቢገለጽም መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑን፣
    - ✓ በአማራ ብሔራዊ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በሞረትና ጅሩ ወረዳ አርሶ አደሩ የጥቁር አፈር ማንጣፈፍ ቴክኖሎጂን በራሱ ባህላዊ ዘዴ እየተጠቀመ እንዳለና የአፈር ማንጣፈፊያ (IBAR-BBM) ቴክኖሎጂ የወረዳውን የአፈር ባህርይና በአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መመለስ ባለመቻሉ በጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑን፣
    - ✓ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ወረዳው ሦስት የአየር ክልል ያለውና የሚዘራበት ወቅትም የተለያየ በመሆኑ ዘር በሚፈልጉበት ጊዜ በወቅቱ ሊቀርብላቸው አለመቻሉን

ከተከለሱ  መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

23. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-
   - ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች እስከ ቀበሌ ድረስ ወርደው በሚያከናውኑት የድጋፍ እና የክትትል ስራ ላይ የተለዩ ጉድለቶች ሲሆኑ ላጋጠሙ ችግሮችም በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ተወርዶ ግብረ መልስ የተሰጠበት፣ በክልልና በዞን ጥብቅ የክትትልና ድጋፍ እርምት እየተወሰደ በመሆኑን፣
   - ✓ እንደ ሞረትና ጅሩ ያሉት አካባቢዎች በአይባር ቢቢኤም ሳይቀር ለማጠንፈፍ አስቸጋሪ የሆኑ አካባቢዎች በመሆናቸው ከባድ የኮትቻ አፈር የሚያጠነፍፍ ቴክኖሎጂ እስኪመጣ ድረስ አርሶ አደሮች ሲጠቀሙበት በነበረው የሽሩቤና ዝቆሽ አሰራር መቀጠሉ የግድ እንደሆነ፣

   ገልፀዋል፡፡

24. ይሁን እንጂ ለረቂቅ ሪፖርቱ በተሰጠው ምላሽ ላይ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ተወርዶ ግብረ መልስ ስለመሰጠቱ፣ በክልልና በዞን ጥብቅ የክትትልና ድጋፍ እርምት እየተወሰደ ስለመሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቀው ያልቀረቡ በመሆኑ፣ በአይባር ቢቢኤም ለማጠንፈፍ አስቸጋሪ የሆኑ የኮትቻ መሬት ያለባቸው አካባቢዎች ላይ ጥቅም የማይሰጡት ቢቢኤሞች ወደሚፈለጉበት አካባቢ እንዲዛወሩ ባለመደረጉ ለሪፖርቱ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡
25. የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት የአካባቢውን ስነ ምህዳርና የአመራረት ዘይቤ እንዲሁም የአርሶ አደሩን ፍላጎት ያላገናዘበ የሚሆንበት ሁኔታ በመኖሩ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ፍላጎት እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ ውጤታማና ወቅቱን የጠበቀ አመራረት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለኢንዱስትሪ የሚሆን ምርት እንዲመረትና የኢንዱስትሪ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፤

26. ለአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ የኢንደስትሪ ግብዓት የሚሆን የሰብል ምርት አርሶ አደሩ እንዲያመርትና ከኢንደስትሪ ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊሰጥና ስለ አፈጻጸሙም በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን በተካሄደ ዳሰሳ ጥናት ላይ በሀገሪቱ ከፍተኛ ምርት ከሚገኝባቸው ሰብሎች አንዱ ስንዴ መሆኑና ይህንንም ጥሬ ዕቃ በመጠቀም በርካታ የዱቄት ፋብሪካዎች ቢመሰረቱም በተለይ ዱረም ስንዴ በበቂ መጠንና ጥራት በሀገር ውስጥ ባለመመረቱ ስንዴ ከውጪ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

28. በተጨማሪም በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ በሚያመርቷቸው ምርቶች ላይ በመመስረት የኤክስፖርትና የኢንደስትሪ ምርቶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግ ቢሆንም ሌሎች ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውሉና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶችን አርሶ አደሩ እንዲያመርት በጥናት ላይ ተመስርቶ የተሰራ ስራ መኖሩን እንደማያውቁ፣
- ✓ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የቢራ ገብስ ለማምረት አቅም ያላቸው ወረዳዎች ተመርጠው አርሶ አደሩ የቢራ ገብስ እንዲያመርት ትምህርት የተሰጠ ቢሆንም ፋብሪካው ለቢራ ገብሱ ያስቀመጠው ዋጋ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት አርሶ አደሩ ለመሸጥ ያልተስማማበት ሁኔታ እንዳለ፣
- ✓ አርሶ አደሩ ከኢንደስትሪው ጋር በበቂ ሁኔታ ትስስር ኖሮት ምርቱን ለማቅረብ የሚያስችል ስራ እንዳልተሰራ፣
- ✓ ስንዴን በተመለከተ ለአርሶ አደሩ የተሻሻለ ዝርያ ሊቀርብለት ባለመቻሉ ለኢንዳስትሪ ግብዓት የሚሆን ስንዴ ማቅረብ እንዳልቻለ እና የማስተሳሰሩ ስራ በሀሳብ ደረጃ እንዳለ እና ተግባራዊነቱ ግን በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ

ገልጸዋል፡፡

29. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ካለፉት ሁለት አመታት ወዲህ በጥናት ላይ ተመስርቶ የአገሪቱን የኢንደስትሪ ዕድገት ለማፋጠን የአግሮ ኢንደስትሪ ፓርኮች በተመረጡ ልማት ቀጠናዎች ለማቋቋም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ከኢንዱስትሪና ንግድ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና ልማት አጋሮች ጋር በመሆን እየሰራ መሆኑን እንዲሁም ትስስሩን ለማጠናከርና ህጋዊነት ማላበስ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የበለጠ ተቀራርቦ መስራትና ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የማይገፋፋ ወጥ መመሪያ ማውጣቱ ላይ በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠ ገልፀዋል፡፡

30. ይሁን እንጂ ካለፉት ሁለት አመታት ወዲህ በጥናት ላይ ተመስርቶ የአገሪቱን የኢንደስትሪ ዕድገት ለማፋጠን ስለተሰራው ስራ የሚያሳይ ማስረጃ ከረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ ጋር አልቀረበም፡፡

31. ለየአካባቢው ተስማሚ በሆነ ሁኔታ የኢንደስትሪ ምርቶች እንዲመረቱ የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሚፈለገው ደረጃ ባለመሰጠቱ በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ላሉ ኢንደስትሪዎች የሚሆኑ የምርት ፍላጎቶችን አርሶ አደሩ በሚፈለገው ደረጃ በጥራትና በብዛት ማምረት እንዳልቻለና የተመረተውም ቢሆን ጥራት የሌለውና በቂ ባለመሆኑ የገበያውን ፍላጎት መሟላት ካለመቻሉም በላይ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ባለመደረጉ የሀገር ውስጥ የቢራ እና የዱቄት ፋብሪካዎች የሚያስፈልጋቸውን የቢራ ገብስና ዱረም ስንዴ ከውጭ እንዲያስመጡ በመደረጉ የውጭ ምንዛሪን ማዳን እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የአርሶ አደሩን ዘመናዊ አሰራሮችንና የግብርና ምርቶች ተጠቅሞ የማምረት ፍላጎት ግንዛቤ ለማሳደግ ዕቅድ ታቅዶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

32. በግብርና ላይ ለተሰማራው ህብረተሰብ ክፍል የግብርና ምርቶችን የማምረት ፍላጎቱና ለምርታማነት ማነቆ የሆነውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት አቀባበል ችግር ለመፍታት የሚያስችል በእቅድ ላይ የተመሰረተ ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ✓ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ኦሞናዳ ወረዳ በተደረገው ውይይት በወረዳው ካሉት 18 ቀበሌዎች ውስጥ 5000 ሄክታር ያላነሰ የኮትቻ አፈር እንዳለ ቢገለጽም የኮትቻ አፈር ልማትን በዘመናዊ መልክ ለማልማት የተያዘ ዕቅድ አለመኖሩን፣
- ✓ በምዕራብ ሸዋ ዞን በኤጀሬ ወረዳ በአርሶ አደር የማሰልጠኛ ማዕከል ለማካሄድ ከታሰበው ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ ስራ ባሻገር በአርሶ አደር ደረጃ በስፋት ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ አለመዘጋጀቱን፣ በወረዳው በሚገኙ ቀበሌዎች የኮትቻ አፈርን በዘመናዊ መልክ ለማልማት የተያዘ ዕቅድ አለመኖሩን፣ ሁሉንም ሰብሎች ሙሉ ለሙሉ በመስመር ለመዝራት የተያዘው ዕቅድ ዝቅተኛ መሆን በተለይ ማሽላን በመስመር ለመዝራት በዕቅድ አለመያዝ እንዲሁም የማዳበሪያ ዕቅድን በተመለከተ በተለይ ዩሪያ በምክረ ሀሳቡ ውጪ ዝቅ አድርጎ ማቀድ፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን የኤጀሬ ወረዳ አሞቱ ቀበሌ የግብአት አስተቃቀድ አቅርቦትና ስርጭት በተሰጠው ስልጠናና ምክረ ሀሳብ መሰረት አለመፈጸሙን ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በአርሶ አደሩ በኩል ያለውን የግብዓት

አጠቃቀም ማነቆዎች ሊፈታ በሚያስችል መልኩ የክትትልና ድጋፍ ስራው በሚፈለገው ደረጃ አለመካሄዱን

ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

34. በመስክ ጉብኝት ወቅት በታዩት ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የስራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች በሰጡት መልስ፡-
    - ✓ ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ከአርሶ አደሩ የአመራረት ዘይቤ፣ ፍላጎትና ለምርታማነት ማነቆ የሆነው የኤክስቴንሽን አገልግሎት አቀባበል ችግሮች ላይ በመነሳት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ጥናት በማካሄድ አለመሆኑን፣
    - ✓ አንዳንድ ቴክሎጂዎች ለምሳሌ የጤፍ በመስመር መዝሪያ፣ ትራክተሮች፣ የመሳሰሉት ሳይፈተሹና የፍላጎት ማሰባሰብ ሳይሰራ እንዲቀርቡ በመደረጉ ውጤታማ ያልሆኑበት ሁኔታ እንዳለ ገልፀዋል፡፡
35. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በተንቀሳቀሱባቸው ወቅቶች በሪፖርቱ ላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በወቅቱ እየፈቱ እና ግብረ መልስ እየሰጡ የሄዱባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን፣ የኮትቻ አፈር ልማትን በተመለከተ በአገር አቀፍ ደረጃ ሰፊ ሽፋን የያዘውን የኮትቻ መሬት እንዳመቺነቱ በተሻለ ደረጃ ምርታማ እንዲሆን ከክልሎች ጋር እየሰሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡
36. ይሁን እንጂ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ከላይ የተገለጸውን መልስ ቢሰጡም ክፍተቶች ተለይተው በወቅቱ እየተፈቱ ግብረ መልስ ስለመሰጠቱ፣ የኮትቻ አፈር ልማትን በተመለከተ ከክልሎች ጋር እየሰሩ ስላሉት ስራ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልቻልንም፡፡
37. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዕቅድ ከመታቀዱ በፊት የአርሶ አደሩን ፍላጎትና ለምርታማነት ማነቆ የሆኑ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አቀባበል ችግሮችን በመለየት አጠቃላይ የሆነ ጥናት አጥንቶ ጥናቱን መሰረት በማድረግ እንዲታቀድ ባለመደረጉ በአርሶ አደሩ ላይ ያሉ የአመለካከት ችግሮችን መለወጥ እንዳይቻል፣ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎች በአርሶ አደሩ ተቀባይነት እንዲያጡና ምርታማነትን ማሳደግ እንዳይቻል አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ያሉ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎችን በተመለከተ፤

38. እያንዳንዱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠርያና መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ እንዲኖረውና ወቅታዊ የሆነ የአየር ሁኔታ ዘገባና ትንበያ መረጃ እንዲያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ያሉ የስራ ኃላፊዎችና አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እንዲሁም በአካል በመገኘት ለማየት እንደተቻለው አስራ ሁለቱ (ዝርዝራቸው በአባሪ ተያይዟል) የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ የሌላቸው መሆኑን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያ በተሟላ መልኩ እንደማይሰጡ እና ምንም የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ሲገልፁ፣ በቀሪዎቹ በአማራ ክልል በሚገኙ አራት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት (በምዕራብ ጎጃም ዞን ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ እና በደቡብ አቸፈር ወረዳ ላሊበላ ቀበሌ እንዲሁም በምስራቅ ጎጃም ዞን በጎዛመን ወረዳ ወንቃ እና የቦ አርጀና ቀበሌ) ሬንጌጅ ብቻ እንዳለና ይህንን መሰረት በማድረግ የተሟላ ባይሆንም የዝናብ ሁኔታ መረጃ ለመስጠት እንደሚሞክሩ ገልጸዋል፡፡

40. እንዲሁም ከብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ስለ በልግና መኸር ዝናብ ቅድመ ትንበያ አገልግሎትን ለመጠቀም የመረጃ ተደራሽነትን መከታተል፣ ውጤታማነቱን መገምገም እና ሰነድ በማዘጋጀት 50 ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑበት ወርክሾፕ ለማካሄድ ታቅዶ እንዳልተከናወነ በ2006 ዓ.ም የግማሽ አመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

41. ስለሁኔታው የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት መልስ በአንዳንድ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ላይ የዝናብ መጠን መለኪያ መ/ቤቱ የሚያስቀምጥበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም ሜትሮሎጂን አስመልክቶ የቀረቡት ሀሳቦች የተቋማቸው ኃላፊነት (Mandate) እስከምን ድረስ እንደሆነ ግምት ውስጥ ያላስገባ እንደሆነና በዚህ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እያከናወናቸው ያሉ የክትትል ስራዎችን መመልከት ያልተቻለ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪ የሜትሮሎጂ አውደ ጥናትን አስመልክቶ የ2006 በጀት አመት ሁለተኛውን የስድስት ወር አፈፃፀም ከግምት ውስጥ ያላስገባ እንደሆነና አውደ ጥናቱ በሁለተኛው ግማሽ አመት እንደተከናወነ ገልፀዋል፡፡

42. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ነሐሴ 2005 ዓ.ም አሻሽሎ ባዘጋጀው የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሥራ መመሪያ ቁጥር 8.1.6 ላይ እያንዳንዱ ማሰልጠኛ ማዕከል መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ ይኖረዋል በሚል የተቀመጠ ስለሆነ በሪፖርት ላይ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ እንዲሁም የሜትሮሎጂ አውደ ጥናትን አስመልክቶ በሁለተኛው ስድስት ወር አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተከናወነ እንደሆነ ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅትም ሆነ ለሪፖርቱ በተሰጠው መልስ ላይ ማስረጃው ሊቀርብ አልቻለም፡፡

43. በማሰልጠኛ ተቋማቱ የተሟላ የሜትሮሎጂ ጣቢያ አለመኖር እና ጣቢያው እንዲደራጅ ከብሔራዊ ሜትሮሎጂ ጣቢያ ጋር በጋራ በመቀናጀት የሚደረግ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን ተቋማቱ በተጠናከረ ሁኔታ የሜትሮሎጂ ጣቢያ እንዳይኖራቸው እና አርሶ አደሩ ትክክለኛና ወቅታዊ የአየር ሁኔታ መግለጫ ማግኘት እንዳይችል ያደረገ ሲሆን፣ ወቅታዊ የአየር ሁኔታ ትንበያ አለመተላለፉ አርሶ አደሮች መረጃውን አግኝተው በትንበያው መሰረት መስራት ያለባቸውን የግብርና ስራ እንዳያከናውኑና አመራረታቸውም ላይ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከል እንዲደራጅ መደረጉን በተመለከተ፤

44. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች ትምህርት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ በማሰባሰብ በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከል (የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን፣ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን፣ የተለያዩ የአረም አይነቶችን፣ የሰብል በሽታዎችን፣ ሰብል አጥቂ ነፍሳትና ተባይ ናሙናዎችን፣ የግብርና ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን) እና ሰርቶ ማሳያ እንዲያደራጁ እና በመረጃ ማዕከልነትም ጭምር ማገልገል እንዲችሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች እገዛ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ክልል፡-

   - ✓ ሰርቶ ማሳያ ከ2.5 አስከ 3 ሄክታር መሆን ሲኖርበት በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ የሚገኙ 12 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የእያንዳንዳቸው የሰርቶ ማሳያ ስፋት 0.5 እስከ 2 ሄክታር የሚደርስ ሲሆን ከአንዱ በስተቀር ቀሪዎቹ አጥር የሌላቸው መሆኑን፣

- ✓ ያሉት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት በሙሉ በቁሳቁስ (ጠረጴዛ፣ ብላክ ቦርድ፣ ቾክ፣ የመሳሰሉት) ያልተሟሉና ሰርቶ ማሳያቸው በሰብል ልማትና ጥበቃ፣ በእንስሳት ሀብት ልማትና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ሥራ ለማከናወን የተከፋፈለ አለመሆንና የሰርቶ ማሳያ ቦታ የሌላቸው መሆኑን፣
- ✓ በዲማ እና መንገሺ ወረዳ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች እንደ የስራ ዘርፉ በአርሶ አደሩ ወይም በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋሙ ማሳ ላይ በሰርቶ ማሳያ ትግበራ የተሻሻሉ አሰራሮችን፣ የማስተማርና የማስፋፋት ስራ በከፊል እየሰሩ አለመሆናቸውን፣

ከመረጃዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡

46. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መኖር ያለባቸውን ቋሚ ኢግዚቢሽኖችን በተመለከተ በ2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መመሪያ ላይ የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን፣ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን፣ የተለያዩ የአረም አይነቶችን፣ የሰብል በሽታዎችን፣ ሰብል አጥቂ ነፍሳትና ተባይ ናሙናዎችን፣ የግብርና ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለኢግዚቢሽኑ በተዘጋጀ ቦታ እንዲያስተዋውቁ የሚል ቢሆንም በናሙና በታዩት ክልሎች ባሉ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ይህንን ማየት አልተቻለም፡፡
47. በናሙና የታዩት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሰርቶ ማሳያዎቹ መሬት የተሟላ ስፋትን ማለትም ከ2.5 እስከ 3 ሄክታር የያዙ አለመሆናቸውን እንዲሁም መመሪያው በሚያዘው መሰረት ሙሉ በሙሉ አስተማሪ በሆነና በተሟላ መንገድ አለመደራጀታቸውን ለዚህም ወጥ የሆነ ድጋፍ አለመደረጉን የገለፁ ሲሆን፣ በሁለቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚገኙ ሰርቶ ማሳያዎች ደግሞ ለተለያዩ ተግባራት እንዲውሉ ለሌላ አካል የተሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
48. ስለሁኔታው የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት መልስ ከአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን በክልሎች በኩል ለሚመለከታቸው አካላት አፋጣኝ መልስ እየሰጠ ሁኔታው በመሻሻል ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ቋሚ ኢግዚቢሽንን በተመለከተ የማዕከላቱ ባለሙያዎች የተለያዩ የሰብል፣ አረምና ተባይ እንዲሁም የግብርና ቁሳቁሶች

በተቻላቸው መጠን ለማሰባሰብ እየጣሩ ያሉበት ሁኔታ መኖሩንና ተከታታይ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. ሆኖም በኦዲቱ ወቅትም ሆነ ለረቂቅ ኦዲቱ ሪፖርቱ ከተሰጠው መልስ ጋር ኢግዚቢሽንን በተመለከተ የተደረገ ተከታታይ ድጋፍ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበልንም፡፡

50. በናሙና ከታዩት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲሁም ከዞንና ከወረዳ የስራ ኃላፊዎች መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ሰርቶ ማሳያ በተሟላ መልኩ አለመኖር፣ ያለውም ትምህርት ሰጪ በሆነ ሁኔታ አለመደራጀት እንዲሁም ሰርቶ ማሳያ የሌላቸው የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መኖራቸው አርሶ አደሩ ማግኘት ያለበትን ዕውቀት እንዳያገኝና አመለካከቱን መቀየር እንዳይችል እንዲሁም በየጊዜው የሚመጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በሰርቶ ማሳያ ላይ ተሞክረው ውጤታቸውን ማየት ባለመቻሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመቀበል እንዲቸገር ያደርገዋል፡፡

## በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ለአርሶ አደሩ በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እና ለልማት ሰራተኞች የብቃት ማረጋገጫ መሰጠቱን በተመለከተ፤

51. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተዘጋጀው የስልጠና ካሪኩለም መሰረት እንዲሆን፣ በአንድ ክፍል ውስጥ ከ20-30 የሚሆኑ ሰልጣኞች ብቻ እንዲሰለጥኑ እንዲሁም የልማት ሰራተኞችን ብቃት በመፈተሽ ማረጋገጥ እንዲቻል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

52. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን በመንገሺ ወረዳ በ15ቱም ቀበሌዎች የሞጅላር (በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ) ስልጠና እና ሌሎችም ስልጠናዎች ያልተጀመሩ መሆኑን፣ በ2005 ዓ.ም በደቡብ ክልል የባለሙያዎችም ሆነ የልማት ሰራተኞች የሙያ ብቃት ምዘና እንዳልተካሄደ ከተከለሱ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

53. በጋምቤላ ክልል የግብርና ልማት አሰራር ሁኔታ ላይ በአራት የባለሙያዎች ቡድን ከተደረገው የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የቡድን አንድ ሪፖርት ላይ በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን የጎደሬ ወረዳ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ባሉባቸው ቀበሌዎች የሞጅላር ስልጠና ጅምር ላይ የነበረ ቢሆንም ሰልጣኞች እስከ መጨረሻ ትምህርቱን ተከታትለው

አለመጨረስና የጨረሱትም ቢሆን ሰርትፊኬት አለማግኘታቸው እንደ ችግር ተጠቁሟል፡፡

54. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች እና አርሶ አደሮች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ወቅታዊና አጫጭር ስልጠና የሚሰጥ እንደሆነና በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠናን ከንድፈ ሀሳብ ጀምሮ እስከ ተግባር ድረስ ለመስጠት የሚያስችል ጅምሩ እንዳለ፣ ነገር ግን የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ከተቋቋሙበት አላማ አንዱ አርሶ አደርን ማሰልጠን ቢሆንም ይህንን አላማ ከግብ ማድረስ እንዳልተቻለ፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል ኮትቾ ሶፋኒ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም ላይ ስልጠናው ተሰጥቶ ሰርትፊኬት የወሰዱበት ሁኔታ ቢኖርም ተከታታይነት ባለው መልኩ እስካሁን የተሰጠ አለመሆኑን፣
- ✓ በናሙና ከታዩት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መካከል በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኘው ከኮትቾ ሶፋኒ ቀበሌ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም በስተቀር ሌሎቹ በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እየሰጡ እንዳልሆነ፣ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ለባለሙያዎች ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት ቅድመ ዝግጅትና በመሳሪያ ልምምድ እንዲያደርጉ የማይደረግ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ተፈታኞች ፈተናውን የማያልፉበት ሁኔታ መኖሩ፣ ያለፉትም ቢሆኑ እየለቀቁ መሆኑን፣
- ✓ ስልጠና ለመስጠት የሚችል የብቃት ማረጋገጫ የወሰደ ባለሙያ በተሟላ ሁኔታ ባለመኖሩ መደበኛ ስልጠና የማይሰጥ መሆኑን፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል በኮትቾ ሶፋኒ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ማለትም 60 አርሶ አደር በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲሰለጥኑ መደረጉን እንዲሁም ስልጠናው በ2006 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑን፣
- ✓ በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ለሚገኙ ባለሙያዎች በ2006 ዓ.ም በክልሉ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም ተግባራዊ ያልሆነበት ሁኔታ መኖሩን፣

አስረድተዋል፡፡

55. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የብቃት ማረጋገጫ ያልወሰደ ባለሙያ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ላይ የማይቀጠርና ቀድሞ ፈተናውን ሳይወስዱ የተቀጠሩትን ለማስፈተን እየተሞከረ ያለበት ሁኔታ እንዳለ፣ ፈተናውን በሚወስዱበት ወቅት የሚወድቁ ተፈታኞችን በተመለከተ አንዳንዴ ኦሬይንቴሽን በተገቢው መልኩ የማይሰጥበት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ነገር ግን ስራው ላይ እስካሉ ድረስ ስራውን ያውቁታል ተብሎ እንደሚገመት እንዲሁም መደበኛ ስልጠናን በተመለከተ የቀድሞ መመሪያ የተቀየረበትና በአዲስ መልኩ ሊሰራ የታሰበበት ሁኔታ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

56. ለመስሪያ ቤቱ በተላከ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በ2006 በጀት አመት በበጀት እጥረት ምክንያት አንዳንድ ክልሎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠታቸውን ተግባራዊ እንዳላዳረጉ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በተላከው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተዘጋጀው የስልጠና ካሪኩለም መሰረት ስለመሆኑና የልማት ሰራተኞችን ብቃት በመፈተሽ ስለመረጋገጡ የሰጡት መልስ የለም፡፡

57. ሆኖም በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ላይ አብዛኛዎቹ የብቃት ማረጋገጫ ያለው የተሟላ ባለሙያ እንደሌላቸው በመታወቁ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

58. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መመሪያው በሚያዘው መሰረት የካሪኩለም ስልጠና ከንድፈ ሀሳብ እስከ ተግባር ድረስ እየሰጠ ባለመሆኑና ድጋፉም የተጠነከረ ባለመሆኑ፣ ለልማት ሰራተኞች የሚሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ ተከታታይነት ያለው ባለመሆኑ እንዲሁም ከቴክኖሎጂው ጋር ሳይተዋወቁ ለፈተና የሚቀርቡበት ሁኔታ በመኖሩ ብቃት ያለው ባለሙያ በማፍራት አርሶ አደሩ ላይ ሊመጣ የሚገባው የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣና የተማረ አርሶ አደር ለመፍጠር የተያዘው አላማ ከግብ እንዲደርስ ማድረግ አያስችልም፡፡

## 2.2 ለአርሶ አደሩ የተሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶለት ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤

### የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

59. ለአርሶ አደሩ በሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስራ ላይ የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገምና ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት እርካታ ያልተገኘባቸውን በመለየት ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

60. ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ሥርዓት መዘርጋቱ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ሥርዓቱ ቢዘረጋም እርካታውን ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በወቅቱ አለመከናወኑ እንደክፍተት የሚታይ መሆኑን፣ የዳሰሳ ጥናት ባልተደረገበት ሁኔታ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች በመቶኛ 80 መድረሱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ የተጠቀሰ መሆኑን እና የደሰሳ ጥናቱ የኦዲት ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንዳልተጠና ለማወቅ ችለናል፡፡

61. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ የዳሰሳ ጥናት ባልተካሄደበት ሁኔታ የአርሶ አደር የኤክስቴንሽን ተገልጋይ ቁጥር ዕድገት እንደ እርካታ መግለጫ ሆኖ ቀርቧል የሚለው መታረም እንዳለበትና በተቋማቸው ስትራቴጂካዊ ግቦች ላይ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር የአገልግሎታቸው ተደራሽነትን የሚገልፅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

62. ሆኖም ግን የደሰሳ ጥናት ባልተካሄደበት ሁኔታ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር በመጨመሩ ብቻ እርካታ ተገኝቷል የሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

63. ለአርሶ አደሩ የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመገምገምና መሻሻል ያለባቸውን አሰራሮች ለማስተካከል እንዲሁም የእርካታውን ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ባለመከናወኑ ችግሮችን በወቅቱ ለይቶ ማሻሻያ ለማድረግና ውጤታማ ስራዎችን ለመቀጠል አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ባልተካሄደበት ሁኔታ የኤክስቴንሽን

ተገልጋይ ቁጥር መጨመርን በመጥቀስ እንደ እርካታ መጨመር ምልክት አድርጎ ማየት ትክክለኛ ግምገማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

## አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በማደራጀት አተገባበሩን በማየት ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤

64. የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለመስጠት እንዲያመች አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በልማት ቡድን፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሁም የምርት እሴት በሚጨምሩ ቡድኖች ማደራጀትና አተገባበራቸውን በማየት እንዲሻሻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

65. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ✓ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በኩታበር ወረዳ የልማት ቡድን እና የ1ለ5 መሪዎች ተማሪዎቻቸውን በመደበኛ ፕሮግራማቸው የማሰባሰብ እና የማወያየት ሥራ ተከታታይነት ያለው አለመሆኑ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን በሀገረ ማርያም ወረዳ ቁም ድንጋይ ቀበሌ የተግባር ስልጠና የወሰዱ የአደረጃጀቱ መሪዎች በወሰዱት የተግባር ስልጠና ልክ ለተማሪዎቻቸው ስልጠናውን ያለማውረድ አቅም ውስንነት መኖሩ በምስራቅ አማራ ክላስተር-2 ቡድን የመስክ መልስ ሪፖርት ላይ መገለፁን፣
- ✓ በአማራ ክልል በአዊ ዞን በዳንግላ ወረዳ አባድራ አጋጋ እና ጉልት አብሽካን ቀበሌ እንዲሁም ደቡብ ጎንደር ዞን በደራ ወረዳ ሽሜ ማርያም እና ወንጨጥ ቀበሌ የክላስተር ቡድኑ በተገኘባቸው በሁሉም ቀበሌዎች 1ለ5ም ሆኑ የልማት ቡድኖች ተሰብስበው ቢወያዩም ከዚህ በፊት በዘልማድ ሲገናኙ ከሚያደርጉት ንግግር የተለየ አጀንዳ ይዘው ችግሮችን ነቅሰው በማውጣት መፍትሔ ከመስጠት ደረጃ ላይ የደረሰ ውይይት እንደማያካሂዱ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ በወይራ አንባ ቀበሌ አርሶ አደሩ በአደረጃጀቱ ወቅታዊ ስራዎች ላይ የመነጋገር ሁኔታ ቢኖርም ደረጃ እየተሰጣጡ መገማገም የሌለ መሆኑና አደረጃጀቱ ውጤታማ እንዳይሆን እንዳደረገ፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በነጋ ጫላ ቀበሌ የመኸር ስራዎችን በሚገባ አደራጅቶ በመረጃ አለመያዝና የአንድ ለአምስት አደረጃጀት የግምገማ ውጤት በማህደር አለማዘጋጀት ከ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የመስክ ክትትል እና ድጋፍ ሪፖርት ላይ መገለፁን፣

- ✓ ከነሐሴ 16-30/2005 ዓ.ም ድረስ በክላስተር ቲም አባላት የተሰሩ ስራዎች ሪፖርት ላይ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ሌሊሳ ዲምቱ እና ቢቂላ ቀበሌ ከታዩ ደካማ ጎኖች የ1 ለ 5 አደረጃጀቱ የግል ስራቸውን እንዳይሰሩ የሚያደርግና ለውይይት የሚደረገውን ስብሰባ ስራ የሚያስፈታ እንደሆነ አድሮጎ የመመልከት የግንዛቤ ችግር መኖሩን፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

66. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአርሶ አደሩ አደረጃጀት በተፈጥሮ ሀብት ስራ ላይ፣ በግብዓት አቅርቦት፣ ስርጭትና አጠቃቀም እንዲሁም በአርሶ አደር በዓል ላይ በመካፈል በኩል የተሻለ ውጤታማ መሆኑን፣ የምርት ዕሴትን በመጨመር ሥራ ላይ ጅምሩ ያለ ቢሆንም ውጤታማ የሆነ ሥራ እየተሰራ እንዳልሆነ፣ አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ የአርሶ አደሩ አደረጃጀት ውጤታማነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ተገምግሞ የመፍትሄ ሀሳብ የተሰጠበት ሁኔታ እንደሌለ አስረድተዋል፡፡
67. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት መልስ፡-
    - ✓ በደቡብ ወሎ ኩታበር ወረዳና በሰሜን ሸዋ ዞን ሀገረ ማርያም ወረዳ ስለ ልማት ቡድንና 1 ለ 5 አደረጃጀት ግንኙነት የተነሳው በክትትላቸው ለይተው የፈቱት መሆኑን፣
    - ✓ መሪ አርሶ አደሮች ለተከታዮቻቸው የሰለጠኑትን ስልጠና ያለማውረድን አስመልክቶ አርሶ አደሮች እርስ በርሳቸው የመማማር ስራ ረጅም ጊዜ የሚወስድና ተከታታይ ድጋፍና ክትትል የሚጠይቅ በመሆኑ ጉድለቶች እየተስተካከሉ እንደሆነ እና
    - ✓ አሁን ያለው አደረጃጀት ውጤታማ እንዳልሆነ የተገለፀውን በተመለከተ ኤክስቴንሽን ስርዓቱ ውስጥ ያሉት አደረጃጀቶች የየአካባቢውን አግሮ ኢኮሎጂ፣ ፋርሚንግ ሲስተም እና ሀገሪቱ ከደረሰችበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ጋር እየተገናዘቡ በየጊዜው እየተሻሻሉ የሚሄዱበት ሁኔታ እየተሰራበት እንደሚገኝ

ገልፀዋል፡፡

68. ነገር ግን በደቡብ ወሎ ኩታበር ወረዳና በሰሜን ሸዋ ዞን ሀገረ ማርያም ወረዳ ስለ ልማት ቡድንና 1 ለ 5 አደረጃጀት ግንኙነት ላይ ያሉትን ችግሮች በክትትላቸው ለይተው የፈቱት መሆኑን ቢገልፁም ይህንን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

69. የተዘረጉት የአርሶ አደር አደረጃጀቶች አተገባበርና ውጤታማነት አጠቃላይ በሆነና ጥናት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ግምገማ ባለመደረጉ እንዲሁም በሁሉም የአደረጃጀት አይነቶች አርሶ አደሩ አለመሳተፉ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት እንዳይችል ያደርጋል፡፡

## በተሰበሰቡና በተቀመሩ ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት ስለመስጠቱ፤

70. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከምርምር የሚወጡ ፓኬጆች፣ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና አሰራሮች  የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሰረት ባደረጉ የደሰሳ ጥናቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ በተዘጋጁት ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት እንዲሰጥና የመጣውን ውጤት በመገምገም ለቀጣይ እንደ ግብዓት መጠቀም እንዲቻል በየደረጃው ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-
   - ✓ ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና በመቀመር ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የቴክኖሎጂውን ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ግብረ መልስ አለመሰብሰብ፣ በተሰራጩት ምርጥ ተሞክሮዎች የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛት የሚገልፅ መረጃ አለመሰብሰቡ፣
   - ✓ በምዕራብ ኦሮሚያ ምስራቅ ወለጋና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከነሐሴ 16-30/2005 ዓ.ም ድረስ የተሰሩ ስራዎች ሪፖርት ላይ በምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ሌሊሳ ዲምቱ እና ቢቂላ ቀበሌ በስንዴና በጤፍ በመስመር መዝራት ላይ ጊዜና ጉልበት ይፈጃል በሚል ግንዛቤ አርሶ አደሩ ፍቃደኛ አለመሆኑ፣
   - ✓ ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2005 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በአማራ፣ ትግራይና ደቡብ ክልሎች ላይ በአፈፃፀም ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አርሶ አደሮች በመለየት በተሻሻለ ፊልም ቀረፃ ማሰራጨትና

በሚሻሻለው የኮትቻ አፈር ትምህርታዊ ፊልም እንዲካተት የማድረግና የማሰራጨት ስራ ያልተከናወነ መሆኑን፣

- ✓ በአማራ ክልል በግብርና ቢሮ የክረምት ስራዎቻችን የሚገኙበት ሁኔታ በሚል በሀምሌ 30/2006 ከተደረገ የመስክ ሪፖርት ላይ በአጠቃላይ ሲታይ በአማራ ክልል በመስመር የመዝራት ቴክኖሎጂ መሻሻል እየታየበት የመጣ ቢሆንም አንዳንድ ዞኖች ግን አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ የታየ ሲሆን፣ ለአብነት ያህል ደቡብ ጎንደር 32%፣ ሰሜን ጎንደር 40%፣ ደቡብ ወሎ 46% መሆናቸውን

ለመገንዘብ ችለናል፡፡

72. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ በፓኬጅ ላይ አጠቃላይ የሆነ ግምገማ ተሰርቶ ድክመትና ጥንካሬው የተለየበት ማስረጃ እንደሌላቸው እና የቴክኖሎጂን ውጤታማነት በመገምገም ዙሪያ ክፍተት መኖሩን፣
- ✓ ፓኬጅን አስመልክቶ ስልጠናዎች በበቂ ሁኔታ የማይሰጡ በመሆኑ የሙያ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣
- ✓ DH 540 እና DH 660 የሚባሉ የበቆሎ ዘሮች ለረጅም ዘመናት ጥቅም ላይ እንደዋሉና ምርታቸው እየቀነሰ እንደመጣ ነገር ግን ይህን ለማሻሻል ምንም የተሰራ ስራ እንደሌለ፣

ገልፀዋል፡፡

73. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት መልስ፡-

- ✓ የዳይሬክቶሬቱ ሰራተኞች በመስክ ጉብኝት ወቅት በቀበሌ በመገኘት ያገኟቸው ችግሮች በወቅቱ መፍትሄ ተሰጥቶባቸው ግብረ መልስ ለዞንና ለክልል የቀረበ መሆኑን፣
- ✓ ግብርና ሚኒስቴር በፓኬጆች ላይ ያሉትን ክፍተቶች በመገምገም በየአመቱ የፓኬጅ ክለሳ የሚያደርግና አዳዲስ ቴክኖሎጂና አሰራሮች እንዲካተቱ እንደሚያደርግ፣
- ✓ የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት በየአመቱ የአሰልጣኞች ስልጠና ለክልሎችና ዞኖች እንደሚሰጥ፣ ስልጠናዎቹ እስከ አርሶ አደር እንዲደርሱ ክትትል

እንደሚያደርግ እንደሁም በፓኬጁ ትግበራ ላይ ለ6 ክላስተር በመከፋፈል ድጋፍና ክትትል እንደሚያድርግ

ገልፀዋል፡፡

74. ይሁን እንጂ፡-
- ✓ በመስክ ጉብኝት ወቅት በቀበሌ በመገኘት ለዞንና ለክልል የሰጡት ግብረ መልስ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣
- ✓ ግብርና ሚኒስቴር በፓኬጆች ላይ ያሉትን ክፍተቶች በመገምገም ክለሳ በማድረግና አዳዲስ አሰራሮችን የማካተት ስራ እንደሚሰራ ገለፀ ቢሆንም በናሙና በታዩት አንዳንድ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ በፓኬጁ ላይ የተደረገ አጠቃላይ ግምገማ የደረሳቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- ✓ በየአመቱ ለክልሎችና ለዞኖች የአሰልጣኞች ስልጠና ስለመሰጠቱ እና ስልጠናው አርሶ አደር ጋር ስለመድረሱ ክትትል ስለመደረጉ እንደሁም በፓኬጁ ትግበራ ላይ ለ6 ክላስተር በመከፋፈል ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣

በሪፖርቱ ላይ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

75. የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ምርጥ ተሞክሮዎችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመቀመርና በመሰብሰብ ሙሉ በሙሉ ማቅረብ አለመቻሉ፣ በተዘጋጁና ወደ አርሶ አደሩ በቀረቡ ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የሚሰጡ ስልጠናዎች ተከታታይነት ያላቸውና ተግባር ላይ የሚያተኩሩ አለመሆናቸው እንዲሁም የፓኬጅ አተገባበር ላይ የሚሰጠው ስልጠና ያመጣውን ውጤት ገምግሞ ለቀጣይ እንደ ግብዓት ባለመቅረቡና ድጋፉ ጠንካራ አለመሆኑ ፓኬጆች ሙሉ ለሙሉ ወደ አርሶ አደሩ እንዳይሰርፁ፣ በታዩ ክፍተቶች የማሻሻያ እርምጃ ተወስዶ የተስተካከለ ፓኬጅ ማስተላለፍ እንዳይቻል እና የአርሶ አደሩን የአመለካከት ችግር መቀየር እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

**የሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ላይ የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤**

76. በግብርና ኤክስቴንሽን በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያ እና በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎች ላይ በእኩል ሁኔታ ሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተጠቃሚነታቸውንም ለማረጋገጥ እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

77. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና የባህልንም ተፅዕኖ መቀነስ ባለመቻሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል ኤክስቴንሽን ላይ የመሳተፍ ችግር እንዳለ፣ በዕቅድ ደረጃ ሴቶች 30 በመቶ ወጣቶች 10 በመቶ ተጠቃሚ ይሁኑ የሚል ቢሆንም ለሴቶች ስልጠና ተዘጋጅቶ ለመስጠት ሲሞከር ወደ ስልጠና የሚወጡበት ሁኔታ ባለመኖሩ ዕቅዱን ተፈፃሚ ለማድረግ እንዳልተቻለ፣
- ✓ በተለይ ሴቶችን ቴክኖሎጂን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ፓኬጅ በቂ ነው ለማለት እንደማያስችል፣
- ✓ ወጣቶችን በተመለከተ በተለይ በ2006 ዓ.ም ተደራጅተው በተለያየ የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ስራ እየተሰራ ቢሆንም የመሬት ፍላጎታቸውን ማሟላት ባይቻልም ወጣቶችን ተሳታፊ ለማድረግ መሬት በኮንትራት ተከራይተው እንዲሰሩ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝ፣
- ✓ በአጠቃላይ በመስክ ስራ ወቅት መረዳት እንደቻልነው ተሳትፎአዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓት ላይ በተገለፀው መልኩ ወጣቶችና ሴቶች ላይ የተሰራው ስራ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ

ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

78. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊ በቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት ምላሽ ሴቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ለብቻቸው የሚደራጁበት ሁኔታ እንዳለና ወጣቶችን በተመለከተ ግብርናው ላይ ፍላጎት እንደሌላቸው፣ በአጠቃላይ ሲታይ የታዩት ችግሮች የሉም ማለት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡

79. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ አልሰጡም፡፡

80. የማህበረሰባችንን ትልቁን ክፍል የሚይዙ ሴቶችና ወጣቶች እንደመሆናቸው መጠን በየዘርፉ ያላቸው ተሳታፊነት የግብርናው ሴክተር እንዲደርስ በሚፈለግበት ደረጃ ባለመሆኑ ለግብርናው ዕድገት መጓተት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## ደረጃዎችን በማውጣት በደረጃው መሰረት የአርሶ አደር ማሰልጠኛዎቹ እንዲሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤

81. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ ደረጃ ሊያወጣና ተግባራዊነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአወጣው ደረጃ ተቋማቱን መሰረት ለማደራጀትና ማሰልጠኛዎቹ የተሟሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች ድጋፍና ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

82. በመስክ ጉብኝት ወቅት በታዩ ክልሎች ያሉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት

- ✓ የማሰልጠኛ ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ በፅሁፍ እንዳልደረሳቸውና አልፎ አልፎ ከወረዳው በሚላክላቸው ቼክ ሊስት የሚጠቀሙ መሆኑን፣
- ✓ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ሊሰጥባቸው በሚገባቸው ሶስት ሙያዎች ማለትም ሰብል፣ ተፈጥሮ ሀብትና እንስሳት ጥበቃ የተሟላ የኤክስቴንሽን ባለሙያ ባለመኖሩ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ባለሙያው ስራ የሚለቅበት ሁኔታ በመኖሩና ተከታታይነት ያለው ስልጠና ለአርሶ አደሩ አለመሰጠቱን፣
- ✓ አንድ ባለሙያ ለበርካታ አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሰጥ በመደረጉ አርሶ አደሩ የተሟላ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረጉ፣
- ✓ ለአርሶ አደሩ የተሟላ ስልጠና ለመስጠት በማሰልጠኛ ተቋማቱ ሊኖሩ የሚገባቸው ካሜራ፣ ወንበሮች፣ የመብራትና የውሀ አገልግሎት፣ ኮምፒውተር፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የተሟላ የእርሻ መሬትና የተግባር ማስተማሪያዎች ያልተሟሉ መሆኑ፣ ለባለሙያዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ቁሳቁስ (መንቀሳቀሻ) ያልተሟሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው፣

ለመረዳት ችለናል፡፡

83. ስለሁኔታው የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የማሰልጠኛ ማዕከላቱ የአሰራር መመሪያ ለክልሎች ወርዶ ወደ ክልሎቹ የሥራ ቋንቋ ተተርጉሞ ለወረዳዎቻቸው ያወረዱበት ሁኔታ እንዳለና የአሰራር ማንዋሉ ያልደረሳቸው ማዕከላት ወረዳዎቻቸውን በመጠየቅ ወደ ተግባር ሊገቡ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

84. ሆኖም በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ከላይ የተጠቀሰውን መልስ ቢሰጡም ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ በፅሁፍ እንዲደርሳቸው ስለመደረጉ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ሊሰጥባቸው በሚገባቸው ሶስት ሙያዎች ማለትም ሰብል፣ ተፈጥሮ ሀብትና እንስሳት ጥበቃ የተሟላ የኤክስቴንሽን ባለሙያ ስለመኖሩና በዚህ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለተደረገው ድጋፍ የተሰጠ መልስ የለም፡፡

85. የተቋቋሙት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች አሟልተው አለመገኘታቸው ተቋማቱ አርሶ አደሩ ሊያመጣ የሚፈለገውን የአመለካከት ለውጥ እንዳይመጣ ከማድረጉም በላይ የምርት እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## አርሶ አደሩ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤

86. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አርሶ አደሩ የምርት ጥራትና እሴትን የሚጨምሩ እንዲሁም ብክነትን በእጅጉ የሚቀንሱ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በግብርና ሚኒስቴር ደብዳቤ ቁጥር ሃ/to 0021/06 ቀን ጥር 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ሪፖርት ላይ፡-

   - ✓ በአማራና ደቡብ ክልሎች ከድህረ-ምርት ክምችት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የምርት ብክነት (በተለይ በነቀዝ ምክንያት) መኖሩ እንደተስተዋለ፣
   - ✓ በድህረ ምርት ክምችት ወቅት ከ20-30% የሚሆነው ምርት የጥራትና መጠን ብክነት እንደሚደርስበትና አብላጫው ብክነት ደግሞ የሚከሰተው በመጀመርያዎቹ ሶስት የክምችት ወራት ውስጥ መሆኑን

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩ ተገልጿል፡፡

88. በኦዲቱ ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ የኮትቻ አፈር ቢቢኤም በመጠቀም፣ የአሲዳማ አፈርን በላቦራቶሪ ምርመራ በመለየት ኖራ የመጠቀም እንዲሁም የጥራጥሬ እህሎችን ምርታማነት ለማሳደግ ማዳበሪያ ከመጠቀም አንጻር የተሰሩ ስራዎችን ከማስተዋወቅ ስራ ባለፈ በተፈለገው መጠን አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ላይ እንዳልሆነ፣
- ✓ ከ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የተደረገ የመስክ ክትትል እና ድጋፍ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በኤጀሬ ወረዳ ሰፊ ሽፋን ያለው ኮትቻ መሬት የሚገኝ ቢሆንም ቢቢኤምን ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ቢሆንም በወረዳው መጋዘን ውስጥ በብዛት ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑን ለማየት መቻሉ፣
- ✓ በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን በከፍተኛ ደረጃ የአሲዳማ አፈር የሚገኝ ሲሆን 3,163 የአፈር ናሙናዎች ለክልል የአፈር ላቦራቶሪ ለምርመራ ተልከው 384 ናሙና ብቻ ውጤታቸው የተመለሰ ሲሆን፣ የደቡብ ክልል ላቦራቶሪ የቀሪ ናሙናዎችን ውጤት በአፋጣኝ ባለማሳወቁና ውጤታቸው ለታወቁ አካባቢዎች የሚያስፈልጋቸውን ኖራ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም ባለማቅረቡ በ2005 አመት የኖራ ርጭት ስራ እና የአሲዳማ አፈር ልማት የተስተጓጎለ መሆኑን፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ሌሊሳ ዲምቱ እና ቢቂላ ቀበሌ የአንዳንድ ሰብሎች ዘር እጥረት እንዳለና ጥያቄ ቢያቀርቡም ምላሽ ያላገኙ መሆኑ፣

89. እንዲሁም 04/13/05 ከተፃፈ የመስክ ሪፖርት ላይ በ2005/06 ምርት ዘመን መኸር አዝመራ ወቅት፡-

- ✓ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ቅምብቢት ወረዳ ላይ በእቅድ ከተያዘው 9,865 ሄክታር ማሳ በመስመር የተዘራው 2,959 ሄክታር 30% እንደሆነ፣ በያያ ጉለሌ ወረዳ በእቅድ ከተያዘው 24,818 ሄክታር ማሳ በመስመር የተዘራው ድርሻ 5,005 ሄክታር 20% ብቻ መሆኑ፣
- ✓ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በቅምብቢት ወረዳ  በዕቅድ ተይዞ ከቀረበው 12,884 ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ ተሰራጭቶ ጥቅም ላይ የዋለው 5,296.5 ኩንታል  41% መሆኑን፣ በያያ ጉለሌ ወረዳ በዕቅድ ተይዞ ከቀረበው 15,284 ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ ተሰራጭቶ ጥቅም ላይ የዋለው 6,597 43% ብቻ መሆኑ፣

- ✓ በአማራ ክልል ኦሮሚያ ብሔረሰብ ዞን በአርጡማ ፉርሲ ወረዳ በዕቅድ ተይዞ ከቀረበው 5,081 ኩንታል ማዳበሪያ የተሰራጨው 1,665 ኩንታል 33% ሲሆን ከዚህ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው 1,063 ኩንታል ብቻ ከተያዘው እቅድ አንጻር የአጠቃቀም ድርሻ 21% መሆኑ

ታይቷል፡፡

90. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ያሉ የስራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-
    - ✓ ፍላጎትና አቅርቦት እንዳልተጣጣመ እንዲሁም የሚቀርቡት ግብዓቶች በተለይ ምርጥ ዘር ላይ (ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ቅምብቢት፣ ኢሉ፣ ኤጀሬ ወረዳዎች እና በአማራ ክልል ደቡብ አቸፈርና ፋርጣ ወረዳዎች) ጥራታቸውን የጠበቁ እንዳልሆኑና በአንዳንድ ወረዳዎች ላይ የጤፍ በመስመር መዝሪያ ቴክኖሎጂ ከእርሻ ጊዜ ዘግይቶ የመጣበት ሁኔታ መኖሩን፣
    - ✓ ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች (መጋዘን፣ ማጨጃ፣ መውቂያ፣ የመሳሰሉት) ላይ የተጠናከረ ስራ ተሰርቷል ማለት እንደማይቻል፣ ለድህረ ምርት ባለሙያ የስራ ድርሻ ያልተቀመጠ እንደሆነ፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂዎች (በመስመር መዝሪያ፣ አፈር ማጠንፈፊያ (BBM) የመሳሰሉት) ሳይጠኑ እየመጡ አርሶ አደሩ ሳይጠቀምባቸው አለአግባብ በመጋዘን ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡



*በመጋዘንና ከመጋዘን ውጪ የተቀመጡ በመስመር መዝሪያና ጥቁር አፈር ማጠንፈፊያ (BBM)*

91. ስለሁኔታው የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ከአለም የምግብ እና እርሻ ድርጅት እንዲሁም ከግብርና ምርምር ጋር በመሆን እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን መኖራቸውን፣
- ✓ ከኮትቻ አፈር ልማት፣ አሲዳማ አፈር ልማትና ከህያው ማዳበሪያ ጋር ተያይዘው የተነሱት በዋነኝነት ከክትትል እና ድጋፍ ሪፖርቶች ላይ የተገኙ በመሆኑ በወቅቱ ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸው የተስተካከሉ መሆናቸውን፣
- ✓ ለአርሶ አደሮች የሚቀርብ ምርጥ ዘር ሀገራችን ያወጣቻቸውን የዘር ጥራት ስታንዳርድ ካሟሉ ብቻ ለአርሶ አደሮች የሚቀርቡ መሆኑን እና የዘር ጥራት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች በአፋጣኝ የዘር አባዥ ካምፓኒ በሌላ ዘር እንዲተካ እንደሚደረግ፣

ገልፀዋል፡፡

92. ይሁን እንጂ፡-

- ✓ ድህረ ምርት ብክነት ላይ ከአለም የምግብ እና እርሻ ድርጅት እንዲሁም ከግብርና ምርምር ጋር በመሆን እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣

- ✓ የክትትል እና ድጋፍ ሪፖርቶች ላይ የተሰጡትን ግብረ መልሶች የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- ✓ ምርጥ ዘር ላይ (ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ቅምብቢት፣ ኢሉ፣ ኤጀሬ ወረዳዎች እና በአማራ ክልል ደቡብ አቸፈርና ፋርጣ ወረዳዎች) ጥራቱን የጠበቀ ምርጥ ዘር እንዳልቀረበላቸው የገለጹ ቢሆንም በረቂቅ ሪፖርቱ መልስ ያልተሰጠ በመሆኑ፣

የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

93. የቅድመ ምርት ቴክኖሎጂ አቅርቦት በቂ በሚባል ደረጃ አለመሆኑ፣ በድህረ ምርት ወቅት ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም አለመቻል የጥራትና የመጠን ብክነት ማለትም (የቀለም፣ የጣዕም፣ የመልክ መቀየር፣ የምግብ ይዘት መቀነስ) ሊያስከትል የሚችል እና ምርቱ ለዘር በሚሆንበት ወቅት ደግሞ የብቅለት መቀነስ፣ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥና የብዙሃኑ አርሶ አደር ገቢ እንዲቀንስ ተፅዕኖ የሚያሳድርበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

## 2.3 የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት በድህረ ገፅና መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

### ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን አቅርቦት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

94. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከክልሎች፣ ከዞኖች፣ ከወረዳዎች እና ከአርሶ አደሩ ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም አምራቾች መረጃዎችን በወቅቱ የሚያገኙበት የመረጃና የኢንፎርሜሽን ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
95. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ላይ፦
    - ✓ በ2005 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎችና የኤክስቴንሽን ማንዋሎች በመ/ቤቱ ዌብ ሳይት እንዲጫኑ ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች ያልተጫኑ መሆኑ፣

- ✓ በኮማንድ ፖስት አማካኝነት የሚሰበሰበው መረጃ በስልክ ጉትጎታ እንጂ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ተዘርግቶ በዘመናዊ አይ.ሲ.ቲ የተያዘ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ፣ የመረጃ ማሰባሰብያ ፎርማት /ቅፅ/ ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ አለመዘጋጀቱ፣
- ✓ የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ በየጊዜው የሚዘጋጁና ተከልሰው የሚወጡ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፓኬጆችና የማስተማሪያ ማንዋሎች ወዘተ በመ/ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ በየወቅቱ እንዲወጡ (እንዲጫኑ) ባለመደረጉ በኢንተርኔት መረጃ ማግኘት ለሚፈልጉ ባለድርሻዎች ተደራሽ ካለመሆኑም በላይ የተጠቃሚ ቁጥርን ለማወቅና አስተያየቶችን ለመቀበል አለመቻሉ ክፍተት መፍጠሩ የተገለጸ ሲሆን በ2005 እና በ2006 ዓ/ም ዕቅዶች ላይ በግልፅ ያልታየ መሆኑን፣
- ✓ ከክልሎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በወቅቱ ያለመድረስ ችግር እንዳለባቸው ከግብርና ልማት ዘርፍ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ታህሳስ 22 ቀን 2005 ላይ መገለጹን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. ስለሁኔታው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀው ምላሽ አልሰጡም፡፡
97. ሚኒስትር መ/ቤቱ ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር ከአርሶ አደሩ ጀምሮ እስከ ሚኒስትር መ/ቤቱ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ከክልሎች ጋር በመተባበር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ ለአርሶ አደሩም ሆነ ለሌሎች ተጠቃሚዎች ወጥ የሆነና ወቅቱን የጠበቀ ትክክለኛ የመረጃ በተሟላ መልክ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

## የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው መመስረታቸውንና በቅንጅት መስራታቸውን በተመለከተ፤

98. በግብርና ልማት የተሰማሩ የተለያዩ አካላትን የሚያገናኙ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ እነዚህን ካውንስሎች ለማጠናከር የሚያስችል አቅም እና ጠንካራ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊቀርብለት ይገባል፡፡
99. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከተገኘ ማስታወሻ ለመረዳት እንደተቻለው በሱማሌ ክልል ከሚገኙ 9 ዞኖች፣ 68 ወረዳዎችና 713 ቀበሌዎች ውስጥ በሦስት ዞኖችና በጅጅጋ ወረዳ የልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስሎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ በሌሎች ዞኖችና ወረዳዎች ያልተቋቋሙ መሆኑ፣
- ✓ የደቡብ ክልል፣ የሲዳማና ጉራጌ ዞኖችና የኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎች ሰነድ ላይ፡-
  - በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ 14 ዞኖች ውስጥ 11 (78%)፣ ከ 136 ወረዳዎች 47 (35%) ካውንስሎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ በ 3,759 ቀበሌዎች በሙሉ ያልተቋቋሙ መሆኑን፣
  - በደቡብ ክልል ከሚገኙ 18 ዞኖች ውስጥ 17 (94%)፣ ከ 265 ወረዳዎች 127 (48%) ካውንስሉን ያቋቋሙ ሲሆን፣ ከ 6,434 ቀበሌዎች ሁሉም ካውንስሉን እንዳላቋቋሙ፣
  - በኦሮሚያ ክልል ካውንስሉን 11 ዞኖች ቢቋቋሙም ጉባኤውን ያካሄዱት አራቱ ብቻ መሆናቸውን፣
  - በደቡብ ክልል ካውንስሉን ካቋቋሙት 17 ዞኖች ውስጥ አስራ አንዱ ጉባኤውን ያካሄዱ ሲሆን፣ 127 ወረዳዎች ጉባኤው የተካሄደው በ 34 ቱ መሆኑን፣
- ✓ በጋምቤላ ክልል በአራት የባለሙያዎች ቡድን ካደረገው የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የቡድን አንድ ሪፖርት ላይ መገንዘብ እንደተቻለው በጋምቤላ ክልል በዲማ እና መንገሺ ወረዳዎች የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል በወረዳ ደረጃ ተለይቶ ያልተቋቋመ ሲሆን ስለአደረጃጀቱና የአተገባበር መመሪያው የግንዛቤ እጥረት እንዳለ

ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

100. በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች ሙሉ ለሙሉ ለማቋቋም ያልተቻለበት ሁኔታ መኖሩን እና በተቋቋሙባቸውም ቦታዎች በዕቅዱ መሰረት ጉባኤውን ለማካሄድ እንዳልተቻለ አስረድተዋል፡፡

101. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ በቀበሌ ደረጃ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች ግድ ማቋቋም ግዴታ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

102. ሆኖም በሪፖርቱ ላይ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በቀበሌ ደረጃ ማቋቋም ግዴታ እንዳልሆነ የገለፁ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቧቸው በተከለሱ ማስረጃዎች ላይ በቀበሌ ደረጃ ካውንስሉ መቋቋም ሲኖርበት እንዳልተቋቋመ የሚያሳዩ በመሆናቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

103. የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በፌደራልና በክልል ደረጃ ቢቋቋምም በዞን፣ በወረዳና ቀበሌዎች የተጠናከረ የማቋቋም ስራ እየተሰራ ባለመሆኑ፣ በቅንጅት መስራት ባለመቻሉና ችግሮች ላይ ለመነጋገር የሚደረጉ ስብሰባዎችም በታቀደላቸው ወቅት የሚካሄዱ ባለመሆኑ ለአርሶ አደሩ የተቀናጀ፣ ችግሮቹን ያስወገደና ውጤታማ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት አላስቻለም፡፡

## አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት እንዲሁም በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ ያለውን ድጋፍ በተመለከተ፤

104. ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል የግብርና ቢሮዎች ዕቅድ በማቀድ ለክልል ባለሙያዎች የስልጠና መድረኮችን አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀትና በተሻሉ ተሞክሮዎች ላይ በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጦችን በማካሄድ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሊደረግ ይገባል፡፡

105. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2004 እና 2005 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ፡-

- ✓ ስራዎች በሚፈለጉበት ወቅት አለመከናወን፣ ይህም ወቅቱን ያልጠበቀ ስልጠና ለክልሎች በመስጠቱ ክልሎች በወቅቱ ሊጠቀሙበት እንዳልቻሉ መግለፃቸውን እንዲሁም በበልግ ወቅት በምሥራቅ ሸዋ ዞን እና በባሌ ዞን ከፍተኛ ሥራ እንዳለ እየታወቀ አብዛኛውን ጊዜ ስልጠና ለባለሙያውም ሆነ ለአርሶ አደሩ በዛን ወቅት ላይ መደረጉ በሥራዎች ላይ እንቅፋት መፍጠሩን፣
- ✓ የተሰጡ ድጋፎችና ክትትሎች ያስገኙትን ፋይዳ ግብረ-መልስ የመሰብሰብ ስራ ማነስ፣ የሚሰጡ ስልጠናዎች ተግባር ነክ ከማድረግ አንፃር (70/30) የሚለውን መርህ በትክክል አለመፈፀም እና የተግባር ስልጠናዎች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሚያሳይ መልኩ በምስል/ በቪድዮ እንዲሁም በመስክ መርጃ መሳሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ አለመቻሉን፣

- ✓ በትግራይ ክልል በሚገኙ 25 ባለሙያዎችና 5 አርሶ አደሮች በእሬትና በበለስ ቅጠል እና በቲማቲም ምግብ አዘገጃጀት እና እሴት የመጨመር ቴክኖሎጂ ላይ የ10 ቀን ስልጠና ለመስጠት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ 2007 ሩብ በጀት አመት ድረስ ያልተከናወነ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል።

106. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በነጋ ጫላ ቀበሌ የግብርና ሚኒስቴር የክትትል ቡድኑ ባደረገው ውይይት ለምርጥ ተሞክሮ ለተመረጡ አርሶ አደሮች ተሞክሮ የመጣበትን ሂደት የሚያሳይ የየወቅቱ መረጃዎችን በአግባቡ አለመያዝ ችግር እንደታየ በ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የመስክ ሪፖርት ላይ ለመረዳት ተችሏል።

107. በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ያሉ የስራ ሃላፊዎች በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ሰብል ኤክስቴንሽንን በተመለከተ ተከታታይነት ያለው ስልጠናም ሆነ የልምድ ልውውጥ መድረክ በማዘጋጀት መማማሩ እንዲኖር የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ አንድ ሰው ብቻ የሚሰለጥንበት ሁኔታ በመኖሩ ተናቦ የመስራቱ ሁኔታ እንደሌለና ባለሙያው ትክክለኛ ለውጥ ሊያመጣ በሚችልበት መልኩ ስልጠናው እንደማይሰጠው፣
- ✓ በእቅድ የተመራ የልምድ ልውውጥ እንደማይከናወን፣ ባለሙያው ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ባለመሆኑ ምክንያት ሙያውን ከማሻሻል እና ወደ ተግባር ከመቀየር አንፃር ክፍተት የፈጠረ መሆኑንና በተግባር የተደገፉ ስልጠናዎች ማነሳቸውን፣
- ✓ የስልጠና ውጤት መገምገም ላይ ክፍተት እንዳለ፣ የሚሰጡት ስልጠናዎች ወቅታቸውን የጠበቁና አስቀድመው የሚሰጡ አለመሆናቸው፣ ስልጠናዎች ከመሰጠታቸው በፊት የፍላጎት ደሰሳ ጥናት ተሰርቶ አለመሆኑ፣
- ✓ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማቱ መካከል የልምድ ልውውጥ መድረክ እንዳልተዘጋጀና በመረጃ የሚያቀርቡት ነገር እንደሌላቸው፣ እንዲሁም የልምድ ልውውጡ የተደረገባቸው ቦታዎችም ቢሆኑ በቂ ናቸው ለማለት እንደማያስችልና የበጀት እጥረት በመኖሩ በሁሉም ላይ የልምድ ልውውጡን ለማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነ

አስረድተዋል።

108. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ የሚከናወኑ ስራዎችን በቪዲዮ በመቅረፅ ዶክመንት የማድረግ ስራ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ክልሎች የተለያዩ ስራዎችን በዶክመንተሪ እየሰሩ እንደሚያዘጋጁ እንዲሁም ዳይሬክቶሬቱ ተሞክሮዎችን ማስፋት ዋናው ስራው እንደመሆኑ መጠን ለልምድ ልውውጥ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በጀት የሚይዝበት ጉዳይ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

109. ነገር ግን በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ የሚከናወኑ ስራዎችን በቪዲዮ በመቅረፅ ዶክመንት የማድረግ ስራ እየተሰራ እንደሆነ ቢገለፅም ለዚህ ማሳያ የሚሆን ማስረጃ አለመቅረቡ እንዲሁም ተሞክሮ ለማስፋት በጀት እንደተመደበ ቢገለፅም በጀቱን በመጠቀም አሉ የተባሉትን ችግሮች ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት ዝቅተኛ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

110. ለክልሎች የሚሰጠው ስልጠና በታቀደለት ጊዜ የማይከናወንበት ሁኔታ በመኖሩና ተከታታይነት ያለው ባለመሆኑ፣ በአንዳንድ ቦታ የተሰጡ ስልጠናዎች አርሶ አደሮቹ ወቅታዊ ስራዎች ላይ በነበሩበት ጊዜ ስለነበር አርሶ አደሩ ስልጠና ላይ መገኘት እንዳይችል እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የክህሎት ማነስ እንዲኖር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የልምድ ልውውጦች በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መካከል በበቂ ሁኔታ አለመካሄዳቸው የተሻሉ ተሞክሮዎችን እርስ በርስ መለዋወጥና መማማር እንዳይቻል አድርጓል፡፡

## በኤክስቴንሽን አፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት አውደ ጥናት መካሄዱን ግብረ መልስ መሰብሰቡንና ጥናት መደረጉን በተመለከተ፤

111. በግብርና ኤክስቴንሽን አሰራርና በአፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ከክልል ባለሙያዎች ጋር በመሆን አውደ ጥናት በማካሄድ፣ ግብረ መልስ በመሰብሰብና በማጥናት ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳብ መስጠትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

112. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና በመቀመር ለተጠቃሚዎች እንዲዳረስ ቢደረግም የቴክኖሎጂውን ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ግብረ መልስ አለመሰብሰብ፣ በተሰራጩት ምርጥ ተሞክሮዎች የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛት የሚገልፅ መረጃ መሰብሰብ አለመቻል የታዩ ክፍተቶች እንደሆኑና የተሰጡ ድጋፎችና ክትትሎች ያስገኙትን ፋይዳ ግብረ መልስ የመሰብሰብ ሥራ ማነስ እንዳለ ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ ለመረዳት የተቻለና

በ2005 ዓ/ም በግልፅ ያልታቀደ ሲሆን በ2006 ዓ/ም ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

113. በፌደራልና በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላት ወጥተው በምርት ላይ ያሉ የበቆሎ፣ የስንዴ፣ የጤፍ፣ የገብስ፣ የሰሊጥና የባቄላ ሰብል ዝርያዎችን አቋምና ውጤታማነት በመስክ ከግብርና ምርምር ማዕከላት እና ከምርጥ ዘር ድርጅቶች ጋር በመገምገም ለቴክኖሎጂ አፍላቂዎች እና አቅራቢዎች ግብረ መልስ ለመስጠት ታቅዶ ይህ ተግባር ሰብሎቹ በመስክ ላይ ባሉበት ወቅት መከናወን የነበረበት ቢሆንም አለመከናወኑን የ2006 የግማሽ አመት አፈፃፀም ሪፖርትን በመከለስ ለመረዳት ችለናል፡፡

114. በምስራቅ ሸዋ ዞን አደአ ወረዳ እንዲሁም ጊምቢቹ ወረዳ በክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ ላይ የወረዳ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚያደርጉትን ክትትልና ግብረ መልስ በጽሁፍ የሚቀመጥበት ዶክመንት አለመኖሩን ለበልግ እና መኸር ምርት በምስራቅ ኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ሸዋ ዞን እና በባሌ ዞን ከተደረገ የመስክ ጉብኝት ሪፖርት ለማየት ችለናል፡፡

115. ስለሁኔታው የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላጋጠሙ ችግሮች በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ወርዶ ግብረ መልስ የሰጠበትና በክልልና በዞን ጥብቅ የክትትልና ድጋፍ እርምት እየተወሰደ መሆኑን፣ በምርት ላይ የሚገኙ ዝርያዎችን ከመገምገም ጋር ተያይዞ የቀረበው የክላስተር ቡድኖች ለደጋ ስራ በመስክ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት በቼክ ሊስታቸው ውስጥ አብረው ይዘውት የሚሰሩት ስራ ስለሆነ አብሮ የተከናወነ ተግባር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

116. ይሁን እንጂ ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በተሰጠው መልስ ላይ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ተወርዶ ግብረ መልስ ስለመሰጠቱ፣ በክልልና በዞን ጥብቅ የክትትልና ድጋፍ እርምት እየተወሰደ ስለመሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቀው ያልቀረቡ በመሆኑ፣ የክላስተር ቡድኖች ለደጋ ስራ በመስክ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት በቼክ ሊስታቸው ውስጥ አብረው ይዘውት የሚሰሩት ስራ እንደሆነ የገለጹ ቢሆንም ስራው የተሰራ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ለሪፖርቱ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

117. በግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም ውጤታማነት ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ከክልል ባለሙያዎች ጋር በጋራ በመፍታት፣ ግብረ መልስ በመሰብሰብና ችግሮቹ ላይ ጥናት በማካሄድ የመፍትሄ ሀሳብ በመስጠት እንዲሁም ተግባራዊ ማድረግ ላይ መሰራት

ያለባቸው ስራዎች በበቂ ሁኔታ ባለመሰራታቸው አርሶ አደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመተግበር የተቸገሩ ከመሆኑም በላይ ያሉ ችግሮችን በጋራ መፍታት እንዳይቻል አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

118. ሀገሪቱ ካላት የግብርናን ፈጣን ዕድገት በዘላቂነት የማረጋገጥ እና የግብርናን ምርትና ምርትማነት የማሳደግ ራዕይ አንፃር የግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም የግብርና ኤክስቴንሽኑ ለአርሶ አደሩ ዘመናዊና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋት ለመጠቀም የሚያስችል የክህሎት ስልጠና፣ የምክር አገልግሎት የገበያና ሌሎች መረጃዎችን መስጠቱንና በልማት አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ክትትልና ድጋፍ መደረጉ ሲገመገም በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- በኦሮሚያ ክልል በግራር ጃርሶ ወረዳ ኮትቻ ሶፋኒ ቀበሌ አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል አካባቢው ከባህር በላይ ከፍታ 2,700 ሜትር በመሆኑ የተካሄደው የጤፍ መዝራት ሙከራ መዘራት ባለበት የመስመር ርቀት መጠን አለመሆኑ እንዲሁም የተዘራው ዘር ከአካባቢው ዝርያ የማይሻልና ለአግሮ ኢኮሎጂው ተስማሚ አለመሆኑን፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በሞረትና ጅሩ ወረዳ አርሶ አደሩ የጥቁር አፈር ማንጣፈፍ ቴክኖሎጂን በራሱ ባህላዊ ዘዴ እየተጠቀመ እንዳለና የአፈር ማጠንፈፊያ (IBAR-BBM) ቴክኖሎጂ የወረዳውን የአፈር ባህርይና በአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መመለስ ባለመቻሉ በጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑን፣
- አርሶ አደሮች በሚያመርቷቸው ምርቶች ላይ በመመስረተ የኤክስፖርትና የኢንደስትሪ ምርቶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግ ቢሆንም ሌሎች ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውሉና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶችን እንዲያመርት በጥናት ላይ ተመስርቶ የተሰራ ስራ መኖሩን እንደማያውቁ፣
- በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የቢራ ገብስ ለማምረት አቅም ያላቸው ወረዳዎች ተመርጠው አርሶ አደሩ የቢራ ገብስ እንዲያመርት ትምህርት የተሰጠ ቢሆንም

ፋብሪካው ለቢራ ገብሱ ያስቀመጠው ዋጋ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት አርሶ አደሩ ለመሸጥ ያልተስማማበት ሁኔታ እንዳለ፣

- ስንዴን በተመለከተ ለአርሶ አደሩ የተሻሻለ ዝርያ ሊቀርብለት ባለመቻሉ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ላለው ኢንዳስትሪ ግብዓት የሚሆን ስንዴ ማቅረብ እንዳልቻለ እና ማስተሳሰሩ ስራ በሀሳብ ደረጃ እንዳለ እና ተግባራዊነቱ ግን በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ፣
- በናሙና ከታዩት አንዳንድ ወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌዎች የኮትቻ አፈርን በዘመናዊ መልክ ለማልማት የተያዘ ዕቅድ እንደሌለ፣ ሁሉንም ሰብሎች ሙሉ ለሙሉ በመስመር ለመዝራት የተያዘው ዕቅድ ዝቅተኛ እንደሆነ በተለይ ማሽላን በመስመር ለመዝራት በዕቅድ አለመያዙና በተለይ ዩሪያ ማዳበሪያ ከምክረ ሀሳቡ ውጪ ዝቅ ተደርጎ የታቀደ መሆኑን፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩ አስራ ስድስት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት አስራ ሁለቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በነሀሴ 2005 አሻሽሎ ባዘጋጀው የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሥራ መመሪያ መሰረት መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ የሌላቸው መሆኑ፣
- በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የሰርቶ ማሳያዎቹ መሬት የተሟላ ስፋትን ማለትም ከ2.5 እስከ 3 ሄክታር የያዙ አለመሆናቸውን እንዲሁም ሁለት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የሚገኙ ሰርቶ ማሳያዎች ደግሞ ለሌላ ተግባር እንዲውሉ ለሌላ አካል የተሰጡ መሆኑን፣
- በናሙና በታዩት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት በቂ ባለሙያ ስለሌላቸው በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እየሰጡ እንዳልሆነ፣ የብቃት ማረጋገጫ ለባለሙያዎች ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት ቅድመ ዝግጅትና በመሳሪያ ልምምድ እንዲያደርጉ የማይደረግ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ተፈታኞች ፈተናውን የማያልፉበት ሁኔታ መኖሩ፣ ያለፉትም ቢሆኑ እየለቀቁ መሆኑን፣
- ሥርዓቱ ቢዘረጋም እርካታውን ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በወቅቱ አለመከናወኑ እንደክፍተት የሚታይ መሆኑን፣
- የአርሶ አደሩ አደረጃጀት በተፈጥሮ ሀብት ስራ ላይ፣ በግብዓት አቅርቦት፣ ስርጭትና አጠቃቀም እንዲሁም በአርሶ አደር በዓል ላይ በመካፈል በኩል

የተሻለ ውጤታማ ቢሆንም የምርት ዕሴትን በመጨመር ሥራ ላይ ጅምሩ ያለ ቢሆንም ውጤታማ የሆነ ሥራ እየተሰራ እንዳልሆነ፣

- በፓኬጅ ላይ አጠቃላይ የሆነ ግምገማ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሰርቶ ድክመትና ጥንካሬው የተለየበት ማስረጃ እንደሌለላቸው፣ የቴክኖሎጂን ውጤታማነት በመገምገም ዙሪያ ክፍተት እንዳለ እና ፓኬጅን አስመልክቶ በበቂ ሁኔታ ስልጠናዎች የማይሰጡ በመሆኑ የሙያ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣
- ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና የባህልንም ተፅዕኖ መቀነስ ባለመቻሉ ከወንዶች እኩል ኤክስቴንሽን ላይ የመሳተፍ ችግር እንዳለ፣ በዕቅድ ደረጃ የተያዘውን ሴቶች 30 በመቶ ወጣቶች 10 በመቶ ተጠቃሚ ለማድረግ ለሴቶች ስልጠና ተዘጋጅቶ ለመስጠት ሲሞከር ለስልጠና የሚወጡበት ሁኔታ ባለመኖሩ ዕቅዱን ተፈፃሚ ለማድረግ እንዳልተቻለ፣
- የማሰልጠኛ ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ በፅሁፍ እንዳልደረሳቸውና በከፍተኛ ሁኔታ የግብርና ባለሙያዎች ስራ የሚለቁበት ሁኔታ በመኖሩ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ለአርሶ አደሩ ለመስጠት አለመቻሉ፣
- የምርጥ ዘር ፍላጎትና አቅርቦት እንዳልተጣጣመ፣ የሚቀርቡት ግብዓቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዳልሆኑ እንዲሁም በአንዳንድ ወረዳዎች ላይ የጤፍ በመስመር መዝሪያ ቴክኖሎጂ ከእርሻ ጊዜ ዘግይቶ የመጣበት ሁኔታ መኖሩን፣
- ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች (መጋዘን፣ ማጨጃ፣ መውቂያ፣ የመሳሰሉት) ላይ የተጠናከረ ስራ ተሰርቷል ማለት እንደማይቻል፣ ለድህረ ምርት ባለሙያ የስራ ድርሻ ያልተቀመጠ እንደሆነ፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂዎች (በመስመር መዝሪያ፣ አፈር ማጠንፈፊያ (BBM) የመሳሰሉት) ሳይጠኑ እየመጡ አርሶ አደሩ ሳይጠቀምባቸው አለአግባብ በመጋዘን ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን፣
- በየጊዜው የሚዘጋጁና ተከልሰው የሚወጡ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፓኬጆችና የማስተማሪያ ማንዋሎች ወዘተ በመ/ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ በየወቅቱ እንዲወጡ (እንዲጫኑ) ባለመደረጉ በኢንተርኔት መረጃ ማግኘት ለሚፈልጉ ባለድርሻዎች ተደራሽ ካለመሆኑም በላይ የተጠቃሚ ቁጥርን ለማወቅና አስተያየቶችን ለመቀበል አለመቻሉ ክፍተት መፍጠሩ፣

- የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል ከክልል ግብርና ቢሮዎች፣ ከግብርና ምርምር ተቋማት፣ በዘርፉ ውስጥ ካሉ የስራ ሂደቶች ከህብረት ስራ ማህበራት፣ ከቡና አዘጋጅ ኢንዳስትሪዎችና በጥቅሉ በግብርና ልማት ዘርፍ ከሚሰሩ ባለድርሻዎች ጋራ በጋራ ባለመታቀዱ የተፈለገውን ያህል የጋራ ተግባራትን ማከናወን አለመቻሉን፣
- በዕቅድ የተመራ የልምድ ልውውጥ እንደማይከናወን፣ ባለሙያው ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ባለመሆኑ ምክንያት ሙያውን ከማሻሻል እና ወደ ተግባር ከመቀየር አንፃር ክፍተት የፈጠረ መሆኑንና በተግባር የተደገፉ ስልጠናዎች ማነሳቸውን፣
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና በመቀመር ለተጠቃሚዎች እንዲዳረስ ቢደረግም የቴክኖሎጂውን ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ግብረ መልስ አለመሰብሰብ፣ በተሰራጨት ምርጥ ተሞክሮዎች የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛት የሚገልፅ መረጃ መሰብሰብ አለመቻል የታዩ ክፍተቶች እንደሆኑና የተሰጡ ድጋፎችና ክትትሎች ያስገኙትን ፋይዳ ግብረ መልስ የመሰብሰብ ሥራ ማነስ እንዳለ

ታውቋል።

119. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል።

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳቦች

120. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን፣ በኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የተደረገው የስራ እንቅስቃሴ ከነበረው በተጠናከረ መልኩ እንዲከናወን፣ ሀገሪቱ የተማረና ቴክኖሎጂን የሚጠቀም እንዲሁም ውጤታማ አርሶ አደር እንዲኖራትና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ችግሮችን ለመፍታት ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት በተለያየ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ አርሶ አደሮችን የአመራረት ዘይቤ መሰረት ያደረገና የአርሶ አደሩን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ከአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ ምርት ለማምረት የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመዘርጋት የኢንደስትሪ ምርቶች እንዲመረቱ እንዲሁም በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ላሉ የሀገር ውስጥ አግሮ ኢንደስትሪዎች የአርሶ አደሩን ምርት እንዲጠቀሙና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች እንዲቀንሱና የውጭ ምንዛሪን ማዳን እንዲቻል ትስስሩ ሊፈጠር ይገባል፡፡
- የተሟላና ትክክለኛ የአየር ሁኔታ ዘገባ ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ይቻል ዘንድ በየክልሉ በሚገኙ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያሟሉ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙላቸው እንዲሁም መረጃውን ለአርሶ አደሩ እንዲሰጡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የተሟሉ እና በውስጣቸው የሚገኙ ሰርቶ ማሳያዎችም መመሪያው በሚያዘው መሰረት የተደራጁ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚያስተዋውቁ የመረጃ ማዕከሎች በመሆን የአርሶ አደሩን የአመለካከት ችግር የሚቀርፉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ሚኒስትር መ/ቤቱ ከክልሎችና በየደረጃው ከሚገኙ የግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራትና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተዘጋጀው የስልጠና ካሪኩለም መሰረት እንዲሆን እና ለልማት ሰራተኞች የሚሰጠው የሙያ ብቃት ምዘና ባልተቆራረጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲሰጥ እንዲሁም ስልጠናውን ያጠናቀቁ አርሶ አደሮች ሰርትፍኬት እንዲያገኙ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና በየደረጃው ከሚገኙ የግብርና ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለአርሶ አደሩ የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማሻሻልና ውጤታማ ለማድረግ የአርሶ አደሩን የግብርና ምርቶች የማምረት ፍላጎትና ችግሮች በመለየት አጠቃላይ ጥናት ሊጠናና በተደረገው ጥናት መሰረትም እርካታ ያልተገኘባቸውን ለይቶ ማስተካከያ በማድረግ አገልግሎቱን ለመስጠት እንዲቻል ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አርሶ አደሩን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሁም የምርት እሴት በሚጨምሩ ቡድኖች በማደራጀትና በማሳተፍ ውጤታማ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም የአደረጃጀቱ ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው በመገምገም እንዲሻሻል ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ከምርምር የሚወጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር ለአርሶ አደሩ እንደ የፍላጎቱ እንዲቀርብና ተሞክሮው እንዲሰፋ እንዲሁም ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይነት ያለውና ከተግባር ጋር የተቀናጀ ስልጠናና ምክር በመስጠት ውጤቱን በመገምገም ለቀጣይ ስራዎች እንደ ግብዓት እንዲያገለግል ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሴቶችና ወጣቶች በግብርና ኤክስቴንሽን በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያና በሞጁላር ስልጠናዎች (በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና) ላይ በእኩል ሁኔታ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በተለይ ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና ያለባቸውን የባህልን ተፅዕኖ ለመቀነስ ለሴቶች በሚዘጋጀው ስልጠና ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና

ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአርሶ አደር የማሰልጠኛ ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ ለሚመለከታቸው አካላት በፅሁፍ እንዲደርስ እና መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ ደረጃ አሟልተው ስልጠናውን እንዲያከናውኑ ሚኒስትር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍ ሊያደርግና ሊከታተል ይገባል፡፡
- አርሶ አደሩ በቅድመ ምርትና ድህረ ምርት ላይ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች የምርት ጥራትና እሴትን የሚጨምሩ እንዲሁም ብክነትን የሚቀንሱ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን አርሶ አደሩ በሰፊው መጠቀም እንዲችል የማስተዋወቅና የማቅረብ ሥራዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተጠናከረ ድጋፍ እና ክትትል ሊደረግ እንዲሁም ውጤታማነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በአይባር ቢቢኤም ለማጠንፈፍ አስቸጋሪ የሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሰራጩ ቢቢኤሞች ወደ ሌላ ተግባር ላይ ሊውሉ ወደሚችሉበት አካባቢ እንዲዛወሩ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የኤክስቴንሽን ክፍሉ ከክልሎች ጋር ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ ስርዓት ሊኖረው፣ በየጊዜው የሚዘጋጁና ተከልሰው የሚወጡ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፓኬጆችና የማስተማሪያ ማንዋሎች ወዘተ በመ/ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ በየወቅቱ እንዲወጡ (እንዲጫኑ) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻልና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ እንዲሁም በግብርናው ላይ ላሉት ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ማምጣት እንዲቻል የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቋቋሙና በልማት አካላቱ መካከል ጠንካራ የስራ ግንኙነት እንዲፈጠር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የክልል ባለሙያዎችም ሆኑ ውጤታማ የሆኑ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት እርስ በእርስ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ መድረክ እንዲኖራቸው ዕቅድ በማቀድና ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ለአርሶ አደሮች የሚሰጠው


የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤት ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በኤክስቴንሽን አሰራሩ ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት እንዲቻል ከክልል ባለሙያዎች ጋር በመተባበር አውደ ጥናት በማዘጋጀትና ግብረ መልስ በመሰብሰብ እንዲሁም ጥናት በማካሄድ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለተግባራዊነቱና ለውጤታማነቱ በተሻለ ሁኔታ ሊሰሩ ይገባል፡፡

121. በመጨረሻም በግብርና ሚኒስቴር እንዲሁም በናሙና በታዩት ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1

# የግብርና ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ወጥ ተከታታይነት ያለው መሆኑን፣ እንዲሁም የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤና ባህል እንዲሁም የዕውቀት ደረጃ መሰረት ያደረገና በስልጠና የተደገፈ መሆኑን መገምገም፤ | 1. እያንዳንዱ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል መሰረታዊ የሆነ የአየር ሁኔታ መቆጣጠርያና መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ እንዲኖረው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2. በተለያየ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚገኘውን የግብርና አመራረት ዘይቤንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አካባቢ ተኮር የኤክስቴንሽን ስልት ተቀይሶ ሊተገበር ይገባል፡፡ |
| | 3. የአለም የግብርና ምርት ፍላጎትን በማጥናት ለአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ ለኤክስፖርትና ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውል ምርትን እንዲያመርት የሚያስችል  የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 4. የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማቱ የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች ትምህርት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ በማሰባሰብ በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከልን እንዲያደራጁ እና በመረጃ ማዕከልነትም ጭምር ማገልገል እንዲችሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እገዛ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 5. በገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በስልጠና ካሪኩለም መሰረት በተዘጋጁ ማስተማሪያዎች መሰረት የንደፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠናን በማጣመር ከመነሻው ጀምሮ እስከ ውጤት ድረስ ስልጠናው እንዲሰጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6. በግብርናው ላይ ለተሰማራውና ለሚሰማራው ህብረተሰብ ክፍል ከግብርናው ጋር የተያያዘውን ፍላጎቱና ለምርታማነት ማነቆ የሆነ የአመለካከት ችግሩን በማጥናት ዕቅድ ሊታቀድና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 7. በሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገምና ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘርጋትና በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት እርካታውን ለማወቅ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 8. የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለመስጠት እንዲያመች አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሁም የምርት እሴት በሚጨምሩ ቡድኖች ማደራጀትና አተገባበራቸውን በማየት እንዲሻሻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ማድረግ ይገባዋል፡፡ |
| | 9. በግብርናው ላይ ለተሰማራው ህብረተሰብ በሙሉ ከምርምር የሚወጡ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ፓኬጆችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን በህብረተሰቡ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት መሰረት በመቀመርና በመሰብሰብ የአርሶ አደሩን ተሞክሮ በማስፋት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተግባራዊነቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10. በተሰበሰቡና በተቀመሩ ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ለመሙላት እንዲያስችል ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት የመጣውን ውጤት በመገምገም ለቀጣይ እንደ ግብዓት መጠቀም እንዲቻል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 11. በግብርናው ላይ ኤክስቴንሽኑ በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያና በሞጁላር ስልጠናዎች በእኩል ሁኔታና ወጥ በሆነ መልኩ ሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲደረጉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትሉን ሊያጠናክር ይገባል፡፡ |
| 2. ለአርሶ አደሩ የተሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶለት ወጥና በሪፖርት የተደገፈ እንዲሁም ግብረ መልስ የሚሰጥበት መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማደራጀትና ለመሟላት የሚያስችል ደረጃዎችን በማውጣት በመመሪያው መሰረት ማሰልጠኛዎቹ የተሟሉ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት በሞጁላር ስልጠና በአንድ ክፍል ውስጥ ከ20-30 የሚሆኑ ሰልጣኞች ብቻ በአንድ ጊዜ የሚሰለጥኑ እንዲሆኑ፣ የሞጁሉን ሙሉ ሰዓት የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ እና በመስክ ላይ በተግባር እንዲያሳዩ እንዲሁም ሰልጣኞቹ ስልጠናቸውን ሲያጠናቀቁ በሰርትፊኬት መመረቅ እንዲችሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14. የልማት ሰራተኞችን የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም በገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማት የሚገኙ አሰልጣኞችን ብቃት በመፈተሽ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 15. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አርሶ አደሩ የምርት ጥራትና እሴትን የሚጨምሩ እንዲሁም ብክነትን በእጅጉ የሚቀኑሱ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍ ማድረግና ውጤታማነቱን መከታተል አለበት፡፡ |
| 3. የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ የመረጃ አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት | 16. ውጤታማ በሆኑ ማሰልጠኛ ማዕከላት የታዩ የተሻሉ የአሰራር ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች ተቋማት ማስተላለፍ እንዲቻል ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. የገበሬ ማሰልጠኛ ተቋማት ለአርሶ አደሩ ወቅታዊ የሆነ የአየር ሁኔታ ዘገባና ትንበያ መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት እንዲያቀርብ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በድህረ ገፅና መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ማሰራጨቱን፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ስር ያሉ የስራ ክፍሎች በመረጃ ተናበው መስራታቸውን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላትና ከልማት አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረግ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 18. የኤክስቴንሽን ክፍሉ ከክልሎች ጋር ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ወቅቱን የጠበቀ መረጃ፣ ምክርና ሙያዊ እገዛ ለክልሎችና ለአርሶ አደሩ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 19. ከግብርና ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እንዲሁም የገበያ ሁኔታና የግብይት ስርዓት ወሳኝ መረጃዎችን አምራቾች በወቅቱ የሚያገኙበትን የመረጃና የኢንፎርሜሽን አቅርቦት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለማሳደግ ወቅታዊ መረጃዎችንና ውጤታማ ተሞክሮዎችን በማዘጋጀት በተለያዩና ተደራሽ በሆኑ መገናኛ ብዙሃን እንዲተላለፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማመቻቸትና ተከታታይነት ባለው መልኩ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 21. በግብርና ልማት የተሰማሩ የተለያዩ አካላትን የሚያገናኙ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው ለመመስረትና ለማጠናከር የሚያስችል አቅም መፍጠር ይገባል፡፡ |
| | 22. በልማት አካላት መካከል ጠንካራ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ እንዲቀርብ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 23. ዕቅድ በማቀድ ለክልል ባለሙያዎች የስልጠና መድረኮችን አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀትና በክልሎች መካከል የልምድ ልውውጦችን በማካሄድ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24. በግብርና ኤክስቴንሽን አሰራርና በአፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ከክልል ባለሙያዎች ጋር በመሆን አውደ ጥናት በማካሄድ፣ ግብረ መልስ በመሰብሰብና በማጥናት ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳብ መስጠትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡ |
| | 25. የሀገር ውስጥ አግሮ ኢንዳስትሪዎች የአካባቢውን አርሶ አደር ምርት እንዲጠቀሙ ትስስር ሊፈጠር ይገባል፡፡ |

አባሪ 3

# በናሙና የታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ዝርዝር

| ተ.ቁ | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ክልሎች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ዞኖች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ወረዳዎች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | | ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ | ሮቢት ቀበሌ (ሬንጌጅ ያለው) |
| | | | አቸፈር ወረዳ | አብችክሊ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | | ላሊበላ ቀበሌ (ሬንጌጅ ያለው) |
| | | ደቡብ ጎንደር ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ፋርጣ ወረዳ | አውዞት ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | | ፀጉር ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | ፎገራ ወረዳ | ሀገረ ሰላም ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | | አንጎኮ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | ምዕራብ ጎጃም ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ጃቢ ጠህናን ወረዳ | አርባይቱ እንስሳ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | ምስራቅ ጎጃም ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ጎዛምን ወረዳ | ወንቃ ቀበሌ (ሬንጌጅ ያለው) |
| | | | | የቦ አርጀና ቀበሌ (ሬንጌጅ ያለው) |
| 2 | ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | ሰሜን ሸዋ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ግራር ጃርሶ ወረዳ | ኮቲቾ ሶፋኒ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | ደገም ወረዳ | አሊዶሮ አቦ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | | ቅምብቢት ወረዳ | ቁምድንጋይ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | ምዕራብ ሸዋ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ኤጀሬ ወረዳ | ኢናፍቱ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ኢሉ ወረዳ | ቢሲ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |
| | | ለአርሲ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ | |
| 3 | ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | ሲዳማ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | ሸበዲኖ ወረዳ | ሳዴቃ ቀበሌ (ሬንጌጅ የሌለው) |